# የነቢይ

# ቃለህ!

በእንዳለ በሺር

2004 ዓ.ም

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| ምዕራፍ አንድ፡-መግቢያና ግለ ተሞክሮ | 1 |
| ምዕራፍ ሁለት፡-የእግዚአብሔር ድምጽ | 9 |
| ምዕራፍ ሦስት፡-የእግዚአብሔር ድምጽ መንገዶች | 12 |
| ምዕራፍ አራት፡-የትንቢትና የነብይነት አገልግሎት በቤተክርስቲያን | 15 |
| ምዕራፍ አምስት፡-የነቢይ የትርጉም ብያኔ | 18 |
| ምዕራፍ ስድስት፡-ፍለጋ ነቢያት | 21 |
| ምዕራፍ ሰባት፡-የነቢያት የጥሪ ማረጋገጫዎች | 24 |
| ምዕራፍ ስምንት፡-የነቢያት የጥሪ መለያዎች | 27 |
| ምዕራፍ ዘጠኝ፡-የነቢያት ዋና ዋና ሚና | 34 |
| ምዕራፍ አስር፡-የነቢያት የድካም ጎኖች | 46 |
| ምዕራፍ አስራ አንድ፡-የነቢያት ተአማኒነት | 52 |
| ምዕራፍ አስራ ሁለት፡-የእውነተኛ ነቢያት ምዘና | 55 |
| ምዕራፍ አስራ ሦስት፡-የሀሰተኛ ነቢያት መገለጫ ባህሪያት | 59 |
| ምዕራፍ አስራ አራት፡-ማጠቃለያና የነቢያት ሥልጠና አስፈላጊነት | 66 |
| ማጣቀሻ መጽሐፍ | 70 |

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያና ግለ ተሞክሮ

ጊዜው ረዘም ብሏል። ከምሰራበት ክፍለ አገር ወደ አደኩበት ከተማ ቤተሰቦቼ ጋር ለእረፍት መጥቼ በአንድ የጸሎት ሥፍራ ቁጥራችን ከሃያ የማይበልጥ አማኞች በወንድማማች ህብረት ተሰብስበን ጸሎት እናደርግ ነበር። የእግዚአብሔር መንፈስ ረድቶን በተለያዩ የጸሎት ርዕሶች ልመናችንን በህብረት ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር ማቅረብ ጀመርን። የጸሎት ማከተሚያ ጊዜያችን ደርሰና «ነቢይ ነች»» ተብሎ በጉባኤው ተቀባይነት ባገኘች አንዲት እህት አማካኝነት ለእኔ ለወንድማችሁ አንድ መልእክት መጣ። እንዲህም አለችኝ «አንተ ወንድሜ  እግዚአብሔር የሰጠህን መንጸር አውልቀህ በራዕይ አያለው እባክህን ወንድሜ መነጽሩን ወደ ዓይንህ መልስ» አለቺኝ።  የዕለቱ ፕሮግራም ወደ ፍጻሜ መጥቶ «ነቢይቱን» በግል ሄጄ «የእኔ እህት እኔ መልእክቱ አልገባኝም አውልቄ ያየሺኝ መነጽር ምን ያመለክታል?» አልኳት። «ነቢይቱም» «አንተው እወቀው ሚስጢሩ ለአንተው ነው አለቺኝ»። ወገኖቼ ይህንን የትንቢት ምሳሌ ትርጉም ለመፍታት ብዙ ማሰላሰል ጀመርኩኝ። የመልእክቱ ሀሳብ ከማነጽ ይልቅ ውስጤን ይረብሸው ጀመር። በበነጋታው ወደምሰራበት ክፍለ አገር በሉንቺን መኪና እየተጓዝኩ «የምን መነጽር?» እያልኩኝ ከራሴ ጋር ሙግት ጀመርኩኝ። ህይወቴን ከየትኛውም ጊዜ ለጌታ ሀሳብ ሰጥቼ በምሰራበት አካባቢ የክርስቶስን ሀሳብ የማገለግልበት ጊዜ ነበር። ለብዙ ዘመን አመኘው የነበረውን መንፈሳዊ ጥማት በእገልግሎት እየተወጣሁ ያለሁበት ጊዜም ነበር። «በነቢይቱ» መልእክት ምላሽና እያሜ አጣሁ። እንደውም ውስጤ በተለየ መረበሽ እየተሞላ ሄደ። ወደ ምሰራበት ክፍለ አገር ከአሰራ ሁለት ሠዓት ጉዞ በኋላ ደረስሁ። ርጩም ወደ መኖሪያ ቤቴ በመሄድ ውስጤን እየረበሸው ያለውን ድምጽ በጾት የጸሎት ኃይል መቃወም ጀመርሁ። ያ «ነቢይቱ» ሴቲት በትንቢት ያለማቺኝ ድምጽ እኔን ከማነጽ ይልቅ ያፈርሰኝ ጀምሯልና።  የዛን ጊዜ በጸሎት ሥፍራ እያለሁ ግልጽ በሆነ ሁኔታ የጌታን ቃል በድምጽ ሰማሁ «በጎቼ ድምጼን ይሰማሉ ይከተሉኛል

በርካታ ሴቶች ምስክርነቶችም እናንተ አንባቢያን ዘንድ አሉ:: በአንድ ወቅት አንዲት በክርስትና ህይወቷና በሥጋዊ ማንነቷ የተባረከች እህት ያጫወተቺኝ አንድ የትንቢት ገጠመኟን ላስታውሳችሁ:: በምድራችን ውስጥ ህብረተሰብን ሁሉ የሚጠቅም አንድ ሰፊ ድርጅት ነበራት:: ይህ ድርጅት ለበርካታ ዓመታት ያህል ትርፋማ ሆኖ ከሰራ በኋላ በአንድ ወቅት በደረሰበት ድንገተኛ ችግር ምክንያት ለስገዳጅ ኪሳራ ውስጥ ወደ መግባት ደረሰ:: ይህንን ዜና የሰሙ በርካታ «ነቢያት» እዚህች እህት ዘንድ እየሄዱ ድርጅቷ ዳግም ትንሳኤ አግኝቶ በክብር ወደ ቀድሞ ስትራፊ ተግባሯ እንደሚመለስ ይተነብዩ ጀመር:: በግምት ቁጥራቸው ሃያ ሁለት የሚደርሱ «ነቢያት» ይህንን የመልካም መገለጫ ትንቢታቸውን አሰሙ:: በመጨረሻም 23ኛው ነቢይ ወደ እርሷ ዘንድ መጥቶ ድርጅቷ በኪሳራ እንደሚመታ ለእርሷ ግን አስደናቂ የጌታ ምህረትና ጥበቃ እንደሚዘንብ ይናገራል:: ጊዜ በንሥር ክንፍ እየበረረ ሄደ:: ሃያ ሁለቶቹ ነቢያት ያሉት ሳይፈጸም የሃያ ሦስተኛው ነቢይ ትንቢት እውን ሆኖ ቀረ::

አንድ የታወሰኝ ሌላ ገጠመኝ ላውጋችሁ:: ጊዜው ከዘጠኝ ዓመት በፊት ይሆናል:: በአንድ ወቅት በአንድ ሥፍራ የአዳር ፕሮግራም ላይ ተነቃቅተን በጸሎት መንፈስ ነበርን:: ከተለያዩ ቤተክርስቲያናት በዚህ የአዳር ጸሎት ላይ ለመሳተፍ ተሰብስበናል:: በዛን ምሽት በርካታ የጸሎት ርዕሶችን ዳሰስን ለመጸለይ እግዚአብሔር አምላክ ረዳን:: ከዋና ዋና የጸሎት ርእሳችን በተጨማሪ በእለቱ አንድ «ነቢይ» ለእያንዳንዳችን የጸሎት ተሳታፊዎች ግላዊ ጸሎት ያደርግልን ዘንድ ጀመረ:: እኔና አንድ ወዳጄን ወደ ጸሎት ሥፍራው የወሰደን ወንድም አጠገባችን ሆኖ የምሽቱን ብርድ ለመቋቋም ያስችለው ዘንድ የጥጥ ጋቢ ራሱን ሳይቀር ተሸፋፍኖ ይጸልያል:: የዕለቱ ተጋባዥ ነቢይ ወደ እርሱ ጠጋ ብሎ ነካውና « አንቺ እህት ጌታ እንዲህ ይልሻል...» አለ:: ሀሳቡን ሳይጨርስ ወዳጃችንም ቀና ብሎ «ባክህ ወንድሜ እኔ ወንድ ነኝ» ብሎ መለሰለት:: በዚህ የቃላት ልውውጣቸው ሁላችንም ድንጋጤ ቀመስ ሳቅ መሳቃችንን አስታውሳለሁ::

እጅግ የሚቀርበኝ የአገልግሎት አጋሬ የሆነ ወንድም በአንድ የጸሎት ፕሮግራም ላይ አንዲት ነቢይት ተነስታ «በዚህ ሁለት ወር ውስጥ ጌታ እግዚአብሔር ለዚህ ወንድም



መኪና እሰጠዋለሁ ይለኛል:: ይህ ትንቢት ባይፈጸም እኔ የጌታ ባሪያ አይደለሁም» ትለዋለች:: ሁለት ወሯ ሞላ:: ሦስትም ወር:: አራትም አምስትም ወር:: የተባለችው መኪና ወደዚህ ወንድም አልመጣችም:: ተስፋ ብቻ ሆና ቀረች:: ልጁ በአንድ ወቅት ምሬት በሞላበት ድምጸት «እነዚህ ነቢያቶች ቢቻላቸው ሌላም ሌላም ብለው ከአምላካችን ጋር ያጣሉናል» ሲል አድምጨዋለሁ::

አንዲት እህት አንድ እንቶኔ የሚባል የወንጌል አገልጋይን እንደምታገባ ጌታ እግዚአብሔር በነቢይ አማካኝነት እንደተናገራት ለሁላችንም በአንድ ወቅት አጫውታን:: ልቧም በዚህ የትንቢት ቃል ተሞልቶ ወንጌላዊውን ለጋብቻ ጠየቀችው:: ወንጌላዊው ግን ጌታ ለእኔ ስላልተናገረኝ አንቺን ማግባት አላስብሁም ብሎ መለሰላት:: ወንጌላዊም ከጥቂት ዓመታት በኋላ ሌላ ልጅ አፍቅሮ አገባ:: በአሁኑ ሠዓት ወንጌላዊው ከሚወዳት ሚስቱ ጋር ተጋብቶ በሠላም መኖር ከጀመረ እነሆ ሠባት ዓመት ሞላው:: ከሚወዳት ሚስቱም ሁለት የሚያማምሩ ልጆችን አፍርቷል:: አሳዛኙ ጉዳይ ግን ያቺ በትንቢት ከነቢይ ዘንድ ወንጌላዊውን በትንቢት ድምጽ እንደምታገባው የተነገራት እህት «ጌታ ቃሉን አያጥፍምና አሁንም በትእግስት እጠብቀዋለሁ:: በልዩ የመስኮት ተአምር እርሱ እንደማገባው የተስፋ ቃል አለኝ:: ለሰው የማይቻል ለእግዚአብሔር ይቻላል» እያለች ትገኛለች:: ወንጌላዊው በሞቀ የትዳር ህይወት በውጪ አገር ከውድ ባለቤቱና ከልጆቹ ጋር እየኖረ ይገኛል:: በየትኛው ክርስቲያናዊ አስተምሮ ተመርኩዛ ያንን ወንጌላዊ ልታገባው ትችላለች?

የነቢያት አገልግሎት በምድራችን መልካም ጅማሬ ቢኖረውም፣ በዛው መጠን እጅግ ግራ የሚያጋቡ ሌሎች አብሰቶችንም እያስተናገደ ይገኛል:: በርካታ ሀሳዊ ነቢያት ወደ ቤተክርስቲያን ሾልከው ገብተዋል:: አንዳንዶቹ አገልግሎቱን እንደ አንድ ፕሮፌሽን አደራረጉን ተክነው የገቢ ምንጭም አድርገውታል:: ትንቢት በመናገር የሌላ ቤተክርስቲያናትን አባላት የሚያስኮበልሉ፣ትንቢት በመናገር የመበለቶችን የውርስ ሀብት የሚበዘብዙ፣ትንቢት በመናገር ልጅ አልባ የሆኑ መሀኖችን የማይፈጸም የትንቢት ቃል እየተናገሩ አንጡራ ሀብታቸውን የሚያሟጥጡ በርካታ ነቢያት በአገራችን ውስጥ እንደ አሸን ፈልተዋል:: ቃላቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ይልቅ

በስሚዎቻቸው ዘንድ ለግዝፈው የእውነተኛይቱን ሃይማኖት ቀነኛ እያበሰሩ የሚገኙ በርካታ ሀሳዊ ነቢያት ተነስተዋል።

እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባ ጉዳይ ቢኖር በዛው መጠን እውነተኛ ነቢያትም በምድራችን ውስጥ ጌታ እግዚአብሔር አበርክቶልናል። ይህ በራሱ ትልቅ አሜንታን ከእኛ ከቅዱሳን ዘንድ ይጠይቃል። ከአስር ዓመት በፊት ከነበርኩበት የድካም ህይወት ወጥቼ ዛሬ እኔ ወንድማችሁ ትንሳኤ ያገኘሁት በነቢያት አገልግሎት ነው። የህይወት መንገዴ በእንቆቅልሽ ሲሞላ ብዙ ጊዜ ከነቢያት ጋር ጸሎት ማድረግ አንደኛው መንፈሳዊ ገጽታዬ ነው። የነቢያት አገልግሎት ለመንፈሳዊ እድገቴ በብዙ ጠቅሞኛል። ነቢያት ለእኛ ክርስትስን እንደ ግል አዳኛችን አድርገን ለተቀበልን ቅዱሳን ብቻ ሳይሆን ከክርስትስ መንገድ ርቀው ለሚገኙ ሠዎች ሁሉ መድሃኒት ያመጣል። አሁን ዘመኑ ጭንቅና ምጥ የበዛበት ዘመን ነው። እያንዳንዱ የዚች ምድር ነዋሪ የጭንቀት ጋኬጆችን በጭንቅላቱ ውስጥ ተሸክሞ ይዞራል። የሥነ አይሀምር ጠቢባን ለዚህ ምላሽ መስጠት ተስኗቸዋል። ለዚህ መድሃኒቱ እግዚአብሔር ለዛታችን ለቤተክርስቲያን ያስነሳቸው ነቢያት እንደሆኑ ለመካድ ምክንያት እንኳን ጠፍቷል።

በታሪክ አጋጣሚዎች ሁሉ እግዚአብሔር አምላክ በነቢያቱ በኩል ሠልካም ፍቃዱን ለሕዝቦቹ አስታውቋል። ዛሬም ነቢያቱን ተጠቅሞ ቤተክርስቲያንን እያነጸ ይገኛል። ለዚህ አገልግሎት በእውነተኛ ፍሬ የተገለጡ ነቢያት ሁሉ ዋጋቸውን ከሾማቸው ከሠራዊት ጌታ ከእግዚአብሔር ይቀበላሉ። ‹‹በእሽቅድምድም ሥፍራ የሚሮጡት ሠሉ እንዲሮጡ ነገር ግን አንዱ ብቻ ዋጋውን እንዲቀበል አታውቁምን? ›› ብሉ ቅዱስ ቃሉ እንደሚናገር (1ኛ ቆሮ 9:24) ።

እውነተኛ ነቢያት በቤተክርስቲያን ውስጥ ፈታኝ ጥያቄ አንስተው ቅዱሳንን በጽድቅ ጉዳይ ዙሪያ ይሞግታሉ። ነቢይ እውነተኛ የጽድቅ መሪ ስለሆነ የጽድቅና የእውነት ጉዳይ ቀናት ሁልጊዜ ይበላዋልና።



ቤተክርስቲያን ያለ ወንጌላዊ እድገቷ የተገታ እንደሆነ ሁሉ፣ ያለ ነብይም ኃጢያትን የመቋቋም ኃይሏ ደካማ ነው። ያለ ጽድቅና ያለ ቅድስና የመንፈሳዊ እድገት ጉዳይ ፈጽሞ አይታሰብምና (1ኛ ቆሮ 12:27-28) ።

እውነተኛ ነቢያት የመንፈሳዊ ብልጥግና ማለድናትም ናቸው። በእነርሱ አገልግሎት ቅዱሳን ወደ አዲስ የህይወት ለቀጣጫ ይገባሉ። መንፈሳዊ ብልጥግናቸውን ከእነርሱ ጥበብ የተነሳ ይምላሉ። ካልተባለሳቸው የህይወት መንገድ ለፈንገጠው ከፍጻሚያቸው ጋር ይገናኛሉ።

እውነተኛ ነቢያት ቅዱሳንን ሲመጣ ካለ አደጋ ያስመልጣሉ። እውነት መላይ ሆኖ በተለየው የክርስቲያን አካሄድ ጣልቃ ገብተው ቅዱሳንን ከጥፋት ያድናሉ። የበግ ለምድ ተጀቡነው ቅዱሳንን ገሬ የሚያጋቡትን አታላዮችን ከመንጋው ለይተው ያወጣሉ። እግዜር ደገፍ ፍርድ ተናገረው ለላቸን ወደ መጣበት ይለዳሉ። ተፈቀም ወደ እኛ ህይወት ይመልሱታል።

እውነተኛ ነቢያት የሌላት ቤተክርስቲያን የኃጢያት ገረምላ መጥች በነጻነት ይጨፍርባታል። ለዚህም ነው ነብይ አልባ የሆኑ ቤተክርስቲያናት የመንፈሳዊ እድገታቸው ጉዳይ በጥያቄ ውስጥ እየገባ የመጣው። እንደውም የዘመናችን ቤተክርስቲያን በሚሊዮን የሚቆጠሩ መጋቢዎች አሏት። ዳሩ ግን የነቢያቷ ቁጥር እጅግ አናሳ ነው። ይህ ያልተመጣጠነ የአገልጋይ ሥርጭት ቤተክርስቲያንን በጽድቅ ተጽእኖ ዙሪያ ለመርዊ ውጤት እንዲታመጣ እንቅፋት ሆኖባታል። ሪክ ጆይነር የነብያት አገልግሎት በሚለው መጽሐፍ ላይ ‹‹የመሪዎችና የጉበኞች (የነቢያት) ጥምረት እንደሚገባው ካልተዋሃደ ድረስ፣ ጉበኞችም መሪዎችም በከንቱ ይደክማሉ ›› ብሏል።

ነቢይ ማለት ምን ማለት ነው? ተግባሩስ? በውኑ በእግዚአብሔር አምላክ የተቀቡ ነቢያት በዚህ ዘመን አሉን? እነዚህና ሌሎች ጥያቄዎች በነቢያት ዙሪያ በአህይምሯችን በየጊዜው ይብለሰለሳሉ። እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ፣በዘመኒቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ በዚህች አነስተኛ ዳሩ ግን እምቅ በሆነች መጽሐፍ ውስጥ

ነቢያትን ስለመልዕክት በርካታ የሥነ-መለኮት ምሁራንም ያላቸውን ግንዛቤ እንጸገርቀዋል። ያንብቡት!



## ምዕራፍ ሁለት

### የእግዚአብሔር ድምጽ

የእኛ አምላክ አምላካዊ ማንነቱን ሲያስተዋውቀን፣ ማንነታችንም ላይ የማንነቱን ሚስጢር ሲገልጽ እጅግ ደስ ይለኛል። እስራኤላውያንን ከግብጽ የባርነት ኑሮ ያስመልጥ ዘንድ በመረጠው በሙሴ ራሱን በሚነድ ቁጥቋጦ ገለጸ። የትውልድ ሁሉ አባት ሁሉ ሆነው እስከ ዛሬ ድረስ በመንፈሳዊ ስሙ ውስጥ እየተዘከሩ ባሉት በእነ አብርሃም፣ በእነ በያዕቆብ በእነ ይስሐቅ በእነርሱ ላይ ባለው አምላካዊ አጀንዳ ሲያሳውቃቸው ተገለጠላቸው። ከእነርሱም ቀጥሎ በተነሱት ለያሉ ቅዱሳን ክብሩ ልዕልናውን ከፍቃዱ ሚስጢር ጋር አዳብሎ ራሱን ተረከላቸው። እንዲሁም በአዲስ ኪዳን የክርስትናን መንፈሳዊ ተግባር ይወጡ ዘንድ በተወሰነላቸው ለሐዋርያት በሙሉ ራሱን በልዩ ልዩ መንገድ አሳወቃቸው።

እግዚአብሔር ድምጹን ለሕዝቡ አሰማ ማለት በሕዝቡ ላይ ያለውን ዘላለማዊ ዓላማ ወይም የተፈጠረበትን የሕይወት ተግባር አሳወቃቸው ማለት ነው። በድምጹ ውስጥ ሆሚጋ የሆነው ፍቃዱ አለ። በድምጹ ውስጥ የፍቃዱ አገልጋዮች ሊሆኑ ለወደዱት ሠዎች ሁሉ የነፍስ እርዳታን ስንቅላቸዋል። ለተፈጠረበት ዋና የሕይወት ፋይዳም መኖር ያስችላቸዋል። የእግዚአብሔርን ድምጽ ለመስማት ስለመልዕክት ዳማዚዮ ፍራንክ የተባለ አገልጋይ ጸሐፊ ‹‹እኔ የእግዚአብሔር ባሪያ ነኝ። ሁልጊዜ ከእርሱ ዘንድ ትእዛዝ ተቀብዬ ተግባሬን መወጣት አለብኝ። ትእዛዙን የምቀበለው በድምጹ ነው። ድምጹ ደግሞ ሁልጊዜ ያሻኛል›› ብሏል።

### የድምጽ ምንጮች

በጊዜው የዚህ ምድር ነዋሪ የሆኑ የእግዚአብሔር ልጆች አራት ዓይነት ድምጽ በሕይወት ዘመናቸው ያደምጣሉ። አራቱም የድምጽ ምንጮች የራሳቸውን ፍቃድና ሀሳብ በሰው ልጆች የልቡና ጆሮ ውስጥ አስደምጠው አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ

ተጽእኖ ማምጣት ይፈልጋሉ፡፡ እነዚህን የድምጽ ምንጮች ከዚህ በታች እንደሚከተለው በጥቂቱና በስሱ እንመልከታቸው፡፡

1. የእግዚአብሔር ድምጽ

እግዚአብሔር ከእኛ ለልጆቹ ሁልጊዜ ድምጹን እያሰማን የልቡን ፍቃድ ያስታውቀናል፡፡ የእርሱ ድምጽ እንደኃያልነቱ የምንጠብቀው የድምጽ አይነት ላይሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ድምጹ የረጋና ሁከት አልባ ነው፡፡ በዝግታ ሁነት የማይገረብጠው ድምጹን ለእኛ ለልጆች ያሰማናል፡፡ በጎቹ ነንና ድምጽ እናውቃለን፡፡ እንከተለዋለንም፡፡

2. የሰይጣን ድምጽ

ሰይጣንም ድምጹን ያሰማናል፡፡ የእርሱ ድምጽ ወደ ዝና፣ ወደ ሀብት፣ ወደ ለስም ከንቱ ነገር ያመራናል፡፡ የእርሱ ድምጽ ጊዜ እየበረረ፣ ጊዜ ጥሉን እየሄደ እንዳለ ያሳስበናል፡፡ ከዚህ የተነሳ ልባችን ያለ እረፍት በተጣደፈ ሁነት ውስጥ ገብቶ የተንቀዠቀዠና የተንከዋከበ ይሆንብናል፡፡ ዘወትር አዘጋጅቶ በሚጠብቀን ጥልቅ ሸለቆ ውስጥም ይጥለናል፡፡ በሌላ አነጋገር የሰይጣን ድምጽ አድማጩን በጊዜ መብረርና በባተሌነት መካከል ባለው ውዝግብ ውስጥ ታንቆ እንዲቀር ያደርገዋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም ይህንን የሰይጣን አብሰት ሳንለተው በርትተን እንድንቃወመው ጠቋሚ ሀሳቡን የሚሰጠን በዚህ ምክንያት ነው (1ኛ ጴጥ 5:9፣ ኤፌ 6:1)፡፡

3. የራስ ድምጽ

ማንነታችንም ለገዛ ራሳችን ድምጽ ያሰማናል፡፡ የራሳችን የሥጋ ፍላጎት እየፈጸምን እንድንኖር ይሞግተናል፡፡ ተላላው ልባችንም ይህንን_የሥጋ ምክር እየሰማ የህይወት ጥሪያችንን ከመልካሙ የእግዚአብሔር ሀሳብ ለይቶ በጠፋው ዓለም ነገር ላይ ብቻ እንድናተኩር ይገፋፋናል፡፡

4. የሌሎች ሠዎች ድምጽ



አንዳንድ ጊዜ ለማን ፍቃድ መኖር እንዳለብን ግራ ይገባናል፡፡ ሠዎች ማለትም ጎረቤቶቻችንን፣ ቤተሰዎቻችን፣ የትዳር አጋሮቻችን የቅርብ ወዳጆቻችን ሁሉም እውቀውም ሆነ ሳያውቁ በራሳቸው የሀሳብ ፍቃድ ውስጥ እንገባ ዘንድ ተጽእኖ ሲያደርጉብን እናገኛቸዋለን፡፡ ዳሩ ግን ማንም ሰው እግዚአብሔር በልቡ ያላደረው አንድ የህይወት አጀንዳ አለ፡፡ ለእርሱ አጀንዳ ብቻ ይኖራል! ይሞታልም፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የእግዚአብሔር ድምጽ መንገዶች

ከላይ የተመለከትናቸው አራት የድምጽ ዓይነቶችና መንገዶች መካከል ከእግዚአብሔር ድምጽ በስተቀር ሁላቸውም ፍጹማን አይደሉም። በተለይ የሰይጣን ድምጽ መቼም ቢሆን ለመልካም ሆኖ አያውቅም። ከሁሉም ድምጾች የአምላካችን የእግዚአብሔር ድምጽ ብቻ ሁልጊዜ እውነተኛና አስተማማኝ ነው። የህይወት ተሞክሮዎቻችንም ለዚህ እውነተኛነቱ ህያው ምስክሮች ናቸው።

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር አምላክ ፍቃዱንና የልብ ምክሩን ወይም ድምጹን በተለያየ መንገድ ለወዳጆቹ ሲገልጽ እናገኛለን። ከዚህ በታች የፍቃዱ መገኛዎች የሆኑትን የድምጽ መንገዶችን እናያለን።

1. መጽሐፍ ቅዱስ

ሐዋሪያው ጳውሎስ ‹‹የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳጽ ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል›› ሲል ተናግሯል (2ኛ ጢሞ 3፡16-17) ። ከዚህ የተነሳ እኛ አማኞች በአንድ አፍ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ድምጽ ነው ብለን የምናምንበት ምክንያት ይኸው ነው።

2. ህልሞቻችንና ተሞክሮዎቻችን

ነቢያት ሀጌ ፣ሚልኪያስና ኢዮኤል ለሰው አይህምር በማይመች የግል ህልሞቻቸው ውስጥ አልፈው የእግዚአብሔርን ድምጽ ወይም ፍቃድ ተረድተዋል (ሚል 3፡6-12) ። አንዳንድ ጊዜ በምናየውና በምናስተውለው ነገር በነፍሳችን ውስጥ መንፈሳዊ የትርጉም ግንዛቤ ይሰጠናል። ለምሳሌ በሠማይ ላይ ንሥር ስትበር ካየን እግዚአብሔር ወዲያው ለአንድ የህይወት ቁም ነገር አንድ ግንዛቤ ወደ ልባችን ያመጣልናል።



በአንድ ወቅት በአንድ ሥፍራ ተቀምጬ የእግዚአብሔር ተስፋ ዘገየብኝ ብዬ እሰላስል ነበር። በተቀመጥኩበት ካፌ ውስጥ ተቀምጬ ሳለሁ ከሬዲዮ የሚስተላለፍ ዘፍን ውስጥ ‹‹ትንሽ ጠብቀኝ›› የሚል የዜማ ግጥም ሐረግ ቃል ሰማሁ። የዋህነትም ይሆናል መሰለኝ በዛን ወቅት ለነበረኝ የሀሳብ ትኩረት እንደ መልስ ሆኖኛል። እግዚአብሔርም ትንሽ ጠብቀኝ የሚለኝ መሰሉ ተሰማኝ።

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ከአእምሮአችን በላይ በሆነ ተአምራታዊ ኩነቶች ፍቃዱን ያስታውቀናል። እግዚአብሔር የለም ብሎ ለሚሞግት እንደ የኮሚኒስት ሥርዓት ተከታይ አንድ የወንጌል አገልጋይ ድንገት በኢየሱስ ስም ብሎ ሲጮህ በኮሚኒስቱ ውስጥ ያለው የክህደት መንፈስ ተንቀሎ ቢወጣ ከዚህ በላይ ለኮምኒስቱ ምን ዓይነት የአምላክ ድምጽ አለ?

3. በተፈጥሮአዊ ክስተቶች

ሠዎች የእግዚአብሔርን ድምጽ ወይም ፍቃድ በህልም፣ በራእይና በተመሰሎ ይቀበላሉ። ህልም ማለት ተኝተን ሳለን በስሜቶቻችን የምንረዳው የምስል ትርጉም ነው። ራእይ ደግሞ ሁሉ ነገር እውን ሆኖ በቀን የምናየው መንፈሳዊ ምስል ነው። ተመሰሎ ደግሞ አእምሮአችን እጅግ ንቁ ሆነ ሳለበአንድ ሥፍራ ሆነን አካባያችንን ወይም መልክ-ሁኔታችንን ዘንግተን የምናየው ሕልም ነው (ዘሁ 12፡6፣ ሐዋ 2፡17-18ን ያንብቡ) ።

4. ነብያቶች

በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር አምላክ የጠለቀ ፍቃዱንና ሀሳቡን በየጊዜው በተነሱ ነብያት አማካኝነት ለወደደው ሰው ድምጹን አሰምቷል። ዛሬም እያሰማ ይገኛል።

እያሉ ቀንም ተቀምጠን ሳለን ነቢይ የነበረ አጋቦስ የሚሉት አንድ ሰው ከይሁዳ ወረደ፡፡ ወደ እኛም መጣና የጳውሎስን መታጠቂያ ወስዶ የገዛ እጁንና እግሩን አስሮ እንዲሁ መንፈስ ቅዱስ ይህ መታጠቂያ ያለውን ሰው አይሁድ በኢየሩሳሌም እንደዚህ ያስሩታል፡፡ በአህዛብም እጅ አሳልፈው ይሰጡታል አለ (ሐዋ 21፡10-11) ፡፡

ነቢያት ከእግዚአብሔር ወደ ሰው መልእክት አስተላላፊ ሰንሰለቶች ናቸው፡፡ በእነርሱ በኩል እግዚአብሔር አምላክ ተግባር የሚፈልጉ መረጃዎችን ለወደደው ሰው ያስተላልፋል፡፡ በእነርሱ በኩል እግዚአብሔር አምላክ የሚያበረታ ቃል ለደከመው ሰው ይልካል፡፡ በእነርሱ በኩል እግዚአብሔር አምላክ በጥፋት መንገድ ያለን ግለሰብ በቀናው መንገድ እንዲሄድ ይመክራል፡፡



ምዕራፍ አራት

## የትንቢትና የነብይነት አገልግሎት በቤተክርስቲያን

በቅርብ ዓመታት ውስጥ የትንቢት አገልግሎት በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በአስገራሚና በሚያመረቃ ሁኔታ እያደገ ይገኛል፡፡ የትንቢት ሥጦታ ለቤተክርስቲያን የተሰጠበት ዋንኛ ምክንያት አማኞችን ለማበረታታትና ለማነጽ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል፡፡ የትንቢት ጸጋ ለሁሉም አማኝ የተሰጠ፣ሁሉም አማኝ ሊለማመደው የሚገባ ጸጋ ነው (1ኛ ቆር 14፡1-3) ፡፡ በርግጥም ሁሉም አማኝ ጸጋውን አብዝቶ እንዲፈልግ የሚነሳሳት ቃል ተሰጥቶታል፡፡ ዳሩ ግን ትንቢት የሚናገር ሁሉ ነቢይ ብሎ መደምደም እንደማይቻል ልብ ይሏል፡፡

አንድ ሰው በመንፈስ ተነሳስቶ በልቡ አንድ ነገር ሞልቶበት በየጊዜው የሚያንጽ ነገር ለቤተክርስቲያን ወይም ለግለሰብ ከተናገረ ይህ ሰው ነብይ ነው ብሎ ወደ ድምዳሜ መድረስ ታላቅ ስሕተት ነው፡፡ በግል የገጠመኝን ጉዳይ ብመሰክር ብዙ ጊዜ በልቤ የሞላውን፣ መልካም መስሎ የታየኝን ምክር ለቅዱሳን ማካፈል እወዳለሁ፡፡ ለአንድ ወንድም በጸሎት ሥፍራ ሆኜ እንድጸልይለት ፍቃዱን ጠይቄ መጸለይ ስጀምር የምጸልየው ጸሎት ከእርሱ የውስጥ ችግር ጋር ተያያዥነት ያለው ሆኖ ያገኘዋል፡፡ ኋላ ጸሎት ጨርሰን ስንነሳ ‹‹አንቺ እኮ የነብይነት ነገር አለብሽ›› ብሎ የሰጠኝን ወንድማዊ አስተያየት አስታውሳለሁ፡፡ የዚህ ወንድም ምኞት መልካም ነበር፡፡ ዳሩ ግን ያሳስተዋለው ጉዳይ ቢኖር ዘመኑ አዲስ ኪዳን መሆኑን ነው፡፡ የአዲስ ኪዳን አማኝ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀ ነው፡፡ በውስጡ የእግዚአብሔር መንፈስ አለበት፡፡ ሲጸልይ መንፈስ ቅዱስ ያግዘዋል፡፡ የጌታንም ሀሳብ በጸሎቱ ውስጥ የማስተሳሰፍ ሚስጢሩ ይኸው ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለተወሰነ አማኝ ብቻ የተሰጠ አይደለም፡፡ የጌታ ኢየሱስ መንፈስ ያለባቸው አማኞች ሁሉ ይህንን ትንቢታዊ አገልግሎት እንደደረሱበት መንፈሳዊ ደረጃ ፋይዳ ያለው መንፈሳዊ መልእክት ለሌላው አማኝ ማስተሳሰፍ ይችላሉ፡፡

ወገኖቼ ትንቢት የተናገረ ሁሉ ነቢይ አይደለም! ከላይ ያቀረብኩላችሁ ምሳሌዎች ለዚህ ሀሳብ ማበልጸጊያ በቂዎች ናቸው። ፈረንጆቹ እንዲህ ያለውን አገልግሎት ኤክዞርቴሽን ይሉታል። በእኔ አፍ ስተረጉመው አነቃሽ-ቃል ብዬዋለሁ። በትንቢትና በአነቃሽ ቃል መካከል ያለው ልዩነት <<ይላል>> የሚለው ቃል ነው። አነቃሽ ቃል ውስጥ የ<<ይላል>> ድሀረ ቅጥያ ቃል አናገኝም። ግለሰቡ መንፈስ ቅዱስ በረዳው መጠን ቤተክርስቲያንን ስለአንድ መንፈሳዊ ጉዳይ ለማነቃቃት ይናገራል። ትንቢት ግን አመጣጡ ከቶውንም ከሠው ፍቃድ አይደለም። ምንጩ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው። ለዚህም ነው ትንቢት የሚናገሩ ቅዱሳን የ<<ይላል>> ቃል መልእክታቸው ማሳረጊያ ላይ የሚጠቀሙት። የእኔን አነቃሽ ቃል በቀላሉ ማረም ሲቻል በ<<ይላል>> ቃል የታጀበውን ትንቢታዊ ቃል ግን ለማረም የሰፋ ስነ-መለኮታዊ እውቀትና መንፈሳዊ ብስለት በብዙ ይጠይቃል።

ማሪዮ ሙሬሎ የተባለ ጸሐፊ <<ትንቢት>> በሚለው መጽሐፍ ላይ <<ትንቢትን ለማረም ጥልቅ መንፈሳዊ ብስለት ያሻል>> ብሏል።

የትንቢት ሥጦታና የነቢይነት አገልግሎት የትርጉምና የአደራረጉ አቅጣጫ እጅግ የተለያየ ነው። ነቢይ በቤተክርስቲያን አመራር ውስጥ ጉልህ ድርሻ ያለው የቤተክርስቲያን ሽማግሌም ጭምር ነው። ነቢይ በቤተክርስቲያን ውስጥ የእግዚአብሔር አፍ ነው። ነቢይ በአንድ የአገልግሎት ጥሪ ላይ ብቻ ታቅቦ የሚቀር ሳይሆን ሁለንተናዊ የቤተክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ጉልህ ድርሻ ያለው የእግዚአብሔር ሰው ነው።

እውነተኛ ነቢይ በሚያመጣው ትንቢታዊ ድምጽ በአሁኑ ዘመን እንዳለው ማወደስ ብቻ አይደለም። ነቢይ በትንቢቱ ያጽናናል፣ ይመክራል፣ ይዘልፋልም። የፍርድንም ቃል ይናገራል። በአንድ ወቅት በአንድ ሥፍራ ተሰብስበን እግዚአብሔርን ስናመልክ ነበር። በመካከላችን ከተማ ውስጥ የሚታወቁ በርካታ ነቢያትም ነበሩበት። በአምልኳችን መካከል ነቢያት እየተነሱ መልካም መልካሙን ይነግሩን ነበር። አንዳንዶቻችን ውጭ አገር ላኩን፣ አንዳንዶቻችንን በአዱኛ ባረኩን፣ አንዳንዶቻችን



በተሳካ ትዳር ባረኩን፣ አንዳንዶቻችንን በመኖሪያ ቤት እድገት ባረኩን። ሁሉም ነቢያት ተነስተው ከእግዚአብሔር ዘንድ ሰማን ያሉትን የትንቢት ድምጽ አሰሙን። በመጨረሻ ላይ አንድ ነቢይ በመካከላችን ፊቱ ጠቋቁሮ አየነው። ብስጭጭት ያለ ይመስላል። እርሱ ደግሞ እንዲጸልይ ተራ ተሰጠው። ጮክ ብሎ በልሳን ከጸለየ በኋላ <<የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። አመንዝራ ሴት ከአመንዝራው ወንድ ጥቅሟን አግኝታ እንደምትሄድ ይሄ ሕዝብ የሚፈልገውን ጥቅም ከእኔ ካገኘ በኋላ ተለይቶኝ የሚሄድ ሕዝብ ነው ይላል >> ብሎ ተቀመጠ። ሠዎች ሁሉ ከመቀመጫቸው ወርደው በእውነተኛ ንሥሓ ተንበርክከው መጸለይ ጀመሩ። የነቢያት አገልግሎት የማወደስ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን እንዲህ ያለውንም የተግሳጽ ትንቢት ያስደምጣል። በደለኛውን ወደ ጽድቅ መንገድ ይመራዋል። በጽድቅ መንፈስም ሞልቶት ከተፈጠረበት ዓላማ ጋር ያገናኘዋለን። ሐዋርያው ጳውሎስ ለዚህ እውነት አስረጂን ያቀርባል።

> ሁሉ ትንቢትን ቢናገሩ ግን የማያምን ወይም ያልተማረ ሰው ቢገባ በሁሉ ይወቀሳል። በሁሉም ይመረመራል። በልቡም የተሰወረ ይገለጣል። እንዲሁ እግዚአብሔር በእውነት በመካከላቸው ነው ብሎ እየተናገረ በፊቱ ወድቆ ለእግዚአብሔር ይሰግዳል (1ኛ ቆሮ 14:24-25) ።

ቢኸል ማይክ የተባለ ጸሐፊ <<በነቢያት ውስጥ ድንቅ የጸጋ ኃይል አለ። ለዚህ ኃይል ሠዎች ሁሉ ይምበረከካሉ>> ብላለች።

## ምዕራፍ አምስት

### የነቢይ የትርጉም ብያኔ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነቢይ (በዕብራይስጥ ነቢ) የሚለው ቃል በስም ገላጭነት አራት መቶ ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ ድርጊት ፈጻሚ ወይም ግስ ሆኖ ደግሞ አንድ መቶ አስር ጊዜ ተጠቅሷል፡፡

ነቢይ የሚለው ቃል በተለያዩ የህብረተሰብ ባህሎች ውስጥ የተለያየ ትርጉም አመላካች ብያኔ ቢኖረውም፣ መጽሐፍ ቅዱሳችን ላይ ግን የትርጉም ምንነቱ በግላጭ ተቀምጧል (ጃይነር ሬከገጽ 15) ፡፡

የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ነቢይ የሚለውን ቃል በስም አመላካችነት እንደሚከተለው ብያኔ ሰጥተውታል፡፡

- በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔርን ድምጽ ተቀብሎ ያለፈውን፣ የዚህኛውን ወይም የመጪውን ጊዜ የሚመለከት መለኮታዊ መልእክት ለሰው የሚያስተላልፍ የእግዚአብሔር መልእክተኛ (ቶምሰን ስቲቭ 298)፡፡
- ሊመጣ ያለውን እንደ ብርቱ ጉዳይ አስቀድሞ መናገር (ሬክ ጃይነር ገጽ 23)፡፡
- ከራሱ መንፈስ ያልመነጨ ሀሳብን ከሠማይ ተቀብሎ የሚያስተላልፍ (ጃኮብ ሲንዲ ገጽ 245)፡፡
- በእግዚአብሔር ፊንታ ሆኖ የሚናገር (ደማዚዮ ፍራንክ ገጽ 30)፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስለ ነቢይ የቀረቡ ብያኔዎች፣

- የሌላው ሰው አፍ ሆኖ የሚነሳ፣



ነቢዩ አሮን የሙሴ አፍ ሆኖ እንደተነሳ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል (ዘጸ 7:1) ፣

እርሱ ስለ አንተ ከህዝቡ ጋር ይናገራል፡፡ እንዲህም ይሆናል፡፡ እሱ አፍ ይሆንልሃል፡፡ (ዘጸ 4:16)

- የእግዚአብሔር አፍ ሆኖ የሚነሳ፣

ነቢዩ በእግዚአብሔር ስም በተናገረ ጊዜ... (ዘዳ 18:22)

ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናገር ... (ዕብ 1:1) ፡፡

- የእግዚአብሔርን ፍቃድና ዓላማ የሚናገር አምባሳደር፣

በእውነት ጌታ እግዚአብሔር ምስጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም (አሞጽ 3:7) ፡፡

የእግዚአብሔር ቃል ወደ አማቴ ልጅ ወደ ዮናስ እንዲህ ሲል መጣ፡፡ ተነሥተህ ወደዚያች ወደ ታላቂቱ ከተማ ወደ ነነዌ ሂድ፡፡ ክፋታቸውም ወደ ፊቴ ወጥቶአልና፡፡ (ዮናስ 1:1-2) ፡፡

በነገራችን ላይ የነቢያት ሚና በጾታ የተገደበ አይደለም፡፡ ሴትም ነቢይት ተብላ ተጠራለች፡፡

‹‹በዚያን ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ ከመንፈሴ አፈስሳለሁ፡፡ ትንቢትም ይናገራሉ (ሐዋ 2:18) ፡፡ በብሉይ ኪዳን ማሪያም ነቢይት ነበረች (ሐዋ 21:8-9)፡፡ ሌሎችም ሌሎችም...፡፡

በዚያን ጊዜ ነቢይቱ የላፊዶት ሚስት ዲቦራ በእስራኤል ትፈርድ ነበር (መሳ 4:4) ፡፡

ከአሴር ወገንም የምትሆን የፋኑኤል ልጅ ሐና የምትባል አንዲት ነቢይት ነበረች (ሉቃ 2፡36) ፡፡



# ምዕራፍ ስድስት

## ፍለጋ ነቢያት

እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን ቢያንስ አንድ ነቢይ ያስፈልገዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የነቢያትን ትንቢት እርግጠኛነት ማረጋገጥ በራሱ አስቸጋሪ ነው፡፡ አንዳንድ ነቢያት ትንቢታቸው የድምፃ ስለሆነ መልእክታቸውን በሚገባ ማረጋገጥ ይከብዳል፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ በነቢያት ደረጃ ያሉ አገልጋዮች ጉባኤ ፊት ቆመው፣ «ምንጩን ለዚህ ሕዝብ ለቀቂያለሁ» ይላሉ፡፡ በእኔ ዘንድ በዚህ ትንቢት ዙሪያ ይሄ ጥያቄ ይቀርባል «የምን ምንጭ?» ፡፡ ሌሎችም እንዲህ ያሉ ትንቢቶች ትንቢት ተናጋሪውን ለመፈተን ይከብዳሉ፡፡ ሰሚውም ግራ እንደተጋባ ወደ ቤቱ ይመለሳል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ትንቢቱ በመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ሲታይ «ትክክል» የሚሆንበት ጊዜ አለ፡፡ ዳሩ ግን ጊዜውን ወይም ትንቢቱ እየተነገረ ካለበት አውድ አንጻር ተቃርኖ ሲፈጥር ይችላል፡፡ ለምሳሌ በርሃብ አለንጋ እየተገረፈ ያለን ጉባኤ «አንተ ሕዝብ አበላሁህ፡፡ አጠጣሁህ፡፡ ጎተራህም ሞላ፡፡ ቤቴን ግን ረሳህ፡፡ አህሉን ወደ ጎተራዬ መልስ» የሚል ትንቢት የሚነገርበትም አጋጣሚ አለ፡፡ ስለዚህ ቤተክርስቲያን የነቢያቶቿን እውነተኛነት በሚገባ ልትፈትን ይገባታል፡፡ የነቢያቶችን ፍሬ በጊዜ ርዝማኔ ይፈተናል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሲናገር «የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ» ብሏል (ማቴ 7፡15-16)፡፡

በማናቸውም ቤተክርስቲያን ውስጥ አንድ ነቢይ የግድ መፈለግ አለበት፡፡ እርሱም እውነተኛ የአገልግሎት ፍሬ ያለው፣ የሚናገረው የእግዚአብሔር ቃል እውነተኛ የሆነ፣ የሚናገረው የእግዚአብሔር ቃል እውነተኛ ሆኖ ተፈትኖ ያለፈ ነቢይ ቤተክርስቲያን በእርግጥም ያስፈልጋታል፡፡

ነቢያት ራሳቸው ዘወትር በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ የሚያስገዙ አገልጋዮች ናቸው፡፡ ብዙ ጊዜያቸውን በጾምና በጸሎት ሥፍራ ያውላሉ፡፡ ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሪት፣ ኃይልና ጥበብ ያሻቸዋል፡፡ ዘወትር ራሳቸውን የነገሮቻቸው የኃይል

ምንጭ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ያስጠጋሉ፡፡ እንዲህ ያሉ ነቢያት ባሉበት ቤተክርስቲያን ውስጥ የነገሮች ምንጭና የመፍትሔ አቅጣጫ ተፈልጎ አይታጣም፡፡

በእርግጥም የክርስቶስ ቤተክርስቲያን በጌታ ምክር የሚሄድ፣ የሚናገረው ቃል እንደሚነድ እሳት የሆነ፣ የሚናገረው ቃል እንደ መዶሻ ሆኖ የሚቀጠቅጥ ነቢይ ያስፈልጋታል፡፡ እነ ኤልያስ፣ እነ ኤልሳዕ፣ እነ አሞጽ፣ እነ ኢዮኤል፣ እነ መጥምቁ ዮሐንስ ህያው ቃል ከአንደበታቸው ይገኝ ነበር፡፡ በመለኮታዊ ኃይል ታግዘውና ተመርተው የዘመናቸውን እንቆቅልሽ ይፈቱ ነበር፡፡

ያለ ምንም ሙግት ነቢያት ለዘመኒቱ ቤተክርስቲያን ያስፈልጋሉ፡፡ ምክንያቱም ነቢያት ቤተክርስቲያንን ያንጻሉ፡፡ መርጥም ወደሚገባት መስመር ውስጥ ተስተካክላ እንድትሮጥ ጥበቡን ያመላክቷታል፡፡ እግዚአብሔር ያለ እነርሱ መገኘት ሙላቱን ለቤተክርስቲያን አይሰጥም፡፡ ነቢያት ለእግዚአብሔር ሕዝብ የበረከት ምንጭና ባለሥልጣን እንደሆኑ የዘዳግም መጽሐፍ እንዲህ ይላል፡፡

> ከወንድሞቻቸው መካከል እንዳንተ ያለ ነቢይ አስነሳላችኋለሁ፡፡ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ፡፡ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል፡፡ በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀለዋለሁ (ዘዳ 18፡18-19) ፡፡

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ያለው ነቢይ ሆኖ ተነስቷል፡፡ ዛሬም በዚህ ዘመን እንዲህ ያለው ነቢይ ያሻናል፡፡ በቤተክርስቲያናችን ውስጥ የምንፈልገው ነቢይ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ለነቢይነት የተፈለገ መሆን አለበት፡፡ የእውነተኛ ነቢይ ምንጭ እግዚአብሔር ነው እንጂ የራስ መነሳሳት አይደለም፡፡ እውነተኛ ነቢይ በራሱ ሳይሆን በጌታ እግዚአብሔር የተቀባ ነው (ኢሳ 6፡1-8) ፡፡ ነቢዩ ኤርምያስን እንመለከት ጥሪው የመጣው ከሠራዊት ጌታ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ እናያለን፡፡

> የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፡፡ በሆድ ሳልሰራህ አውቄሃለሁ፡፡ ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ፡፡ ለአህዛብም ነቢይ አደርጌሃለሁ፡፡ እኔም ወዮ ጌታ እግዚአብሔር እነሆ ብላቴና ነኝና እናገር ዘንድ አላውቅም አልሁ፡፡ እግዚአብሔር ግን እንዲህ አለኝ ‹‹ወደምልክህ ሁሉ ዘንድ ትሄዳለህና፡፡ የማዝዝህንም ሁሉ ትናገራለህና፡፡ ብላቴና ነኝ አትበል፡፡ እኔ አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና፡፡ ከፊታቸው አትፍራ ይላል እግዚአብሔር፡፡ እግዚአብሔርም እጁን ዘርግቶ አፌን ዳሰሰ፡፡ እግዚአብሔርም ፡-እነሆ ቃሌን በአፍህ ውስጥ አኖሬያለሁ፡፡ እነሆ ትነቅልና ታፈርስ ዘንድ፣ ታጠፋና ትገለብጥ ዘንድ፣ ትሠራና ትተክል ዘንድ በአህዛብና በመንግስታት ላይ ዛሬ አደርጌሃሁ አለኝ (ኤር 1፡4-10)፡፡



ነቢዩ አሞጽን እግዚአብሔር ለነቢይነት ሲጠራው እርሱ ደግሞ ወደ ግል ሥራው እየተንቀሳቀሰ ነበር፡፡ አንድም ቀን ነቢይ የመሆን ፍላጎት አድርበት አያውቅም፡፡ ከዛም ባሻገር በብሉይ ዘመን እንደነበረው ወግ የዘር ግንዱ ከነቢያት ወገን አልነበረም፡፡

> አሜስያስም አሞጽን፡- ባለ ራእዩ ሆይ ሂድ ወደ ይሁዳ ምድር ሽሽ፡፡ በዚያም እንጀራህን ብላ፡፡ በዚያም ትንቢትን ተናገር፡፡ …አሞጽም መልሶ አሜሲያስን አለው ‹‹እ ላም ጠባቂ፣ዋርካ ለቃሚ ነኝ እንጂ ነቢይ ወይም የነቢይ ልጅ አይደለሁም፡፡ እግዚአብሔርም በጎችን ከመከተል ወሰደኝ፡፡ እግዚአብሔርም ሂድ ለሕዝቤም ለእስራኤል ትንቢት ተናገረኝ አለኝ (አሞጽ 7፡14-15) ፡፡

የነቢያት ጥሪ ከላይ እንደተመለከትነው የጥሪው ምንጭ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ነቢይነት የእግዚአብሔር ሉዓላዊ አጠራር ነው፡፡ አጠራሩ በማንነትና በምንነት ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡ እርሱ እግዚአብሔር የወደደውን ጠርቶ ነቢይ አድርጎ በሕዝቡ ላይ ይቀባል፡፡ ጥሪው በተጠራው ዘንድ ልክ እንደ ነቢዩ አሞጽ እንደሆነበት ድንገተኛ ጥሪ ሊሆን ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

### የነቢያት የጥሪ ማረጋገጫዎች

በክርስትና የእምነት ሥርዓት ውስጥ ከእግዚአብሔር የሆነ ጥሪ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ያለ ጥሪ በአገልግሎት ላይ መሰማራት እብደትም ሥፍናም ይሆናል፡፡ በተለይ ለነቢያት አገልግሎት የጥሪ ጉዳይ ትልቁን ሥፍራ ይይዛል፡፡ በእግዚአብሔር ስምሳክ ሳይጠሩ ራስን በነቢይነት ማሀረግ መሾም፣ በራስና በቤተክርስቲያን ላይ ትልቅ አደጋ እንደመፍጠር ነው፡፡

አንድ ነቢይ ጥሪው ልክ መሆኑ የሚታወቀው በተናገረው ቃል ወይም መልእክት ልክ ትክክለኛነት ላይ ነው፡፡ ለዚህ ጥሪ ምሳሌ የሚሆነን ነቢዩ ሳሙኤል ይሆናል፡፡ *‹‹ሳሙኤልም አደገ፡፡ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረ፡፡ ከቃሉም አንዳች በምድር ላይ አይወድቅም ነበር፡፡ እስራኤልም ሁሉ ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ድረስ ሳሙኤል ለእግዚአብሔር ነቢይ ይን ዘንድ የታመነ እንደሆነ አወቀ››* (1ኛ ሳሙ 3:19-18) ፡፡

የጥሪ ምንጩ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር የሆነ ጥሪ በሠዎች ዘንድም ተቀባይነት ያገኛል፡፡ ሰዎች የማይቀበሉት ጥሪ ምንጩ ሠዋዊና በራስ ተነሳሽነት የተደረገ ሹመት እንደሆነ ያሳያል፡፡

እውነተኛ የነቢይነት ጥሪ ያለባቸው ነቢያት የሚከተሉት ብርቱ ምልክቶች ይታዩባቸዋል፡፡

- ለእግዚአብሔር ፍቃድ ቀናዒ መሆን፣
- የእግዚአብሔርን እቅድ አስቀድሞ የማወቅ መንፈሳዊ ብቃት፣
- በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ለመሆን፣



ጥሪ ያለው ነቢይ በዝግጅቱም ይታወቃል፡፡ በእግዚአብሔር ጥሪ የተደረገላቸው ነቢያት ከጥሪያቸው በፊት በቂ ዝግጅት ያደርጋሉ (እያወቁም ሆነ ሳያውቁ)፡፡ አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ጥሪና የአገልግሎት ጅማሬ ዘመን ሰፊ ጊዜ ይወስዳል፡፡ እንዲህ ጊዜ የሚወስድ ዝግጅት የተፈተነ ትእግስት ይፈልጋል፡፡

ከጥሪ በኋላ የሞትና የመቀበር ጊዜ በተጠራው ህይወት ያልፋል፡፡ ይህ ነው ታዲያ የዝግጅት ጊዜ ተብሎ የሚታወቀው፡፡ በዚህ የህይወት ቆይታ ውስጥ የጥሪ ጉዳይ በተጠራው ዘንድ የሞተ ሆኖ ሊሰማ ይችላል፡፡ በጥሪና በአገልግሎት ጅማሬ መካከል ያለው የጊዜ ርዝማኔ ማንነትን የመተው ጊዜ ነው፡፡ ትእቢተኛው ትእቢቱን ይተዋል፡፡ ኩራተኛው ኩራቱ ይለቀዋል፡፡ በዚህ መካከል የጥሪ ጉዳይ ለተጠራው ዘበት ሆኖ ይሰማዋል፡፡ ዳሩ ግን ነገሮች ባሉበት ቦታ አይቀጥሉም፡፡ የንጋት ጊዜም አለ፡፡ የጥሪ ጉዳይ በልብ ውስጥ እንደ ማለዳ ብርሃን ወገግታውን እየጨመረ ይመጣል፡፡ በአንድ የአገልግሎት አጋጣሚ ላይ የጥሪ ጉዳይ ሙሉ ህይወት አግኝቶ ማንሰራራት ይጀምራል፡፡

ለነቢይነት የተጠራችሁ አገልጋዮች በሙሉ ይህንን የቅድሚያ ዝግጅት ለመግጠም ዝግጁዎች ናችሁ? ይኸውላችሁ ውርደትን ታውቁት ይሆናል፡፡ በጥሪ ዝግጅት መካከል ግን ኃይል ጨምር ይመጣባችኋል፡፡ መናቅን ታውቁት ይሆናል፡፡ በጥሪ ዝግጅት መካከል ግን ኃይል ጨምር ይመጣባችኋል፡፡ መቸገርን ታውቁ ይሆናል፡ በጥሪ ዝግጅት መካከል ግን ኃይል ጨምር ይመጣባችኋል፡፡

ነቢይ ማለት በምድር ላይ የእግዚአብሔር አፍ ማለት ነው፡፡ በእርግጥም እውነተኛ የአምላክ አፍ ይሆን ዘንድ፣ በመከራ ውስጥ አልፎ አርጌው ሰዋዊ ማንነቱ በእግዚአብሔራዊ ማንነት ይቀየራል፡፡ ትህትና ወደ ነፍሱ ዘልቃ ትገባለች፡፡ ያን ጊዜ እግዚአብሔርን ሊያገለግል ብቁ ሆኖ ይቀርባል፡፡

እግዚአብሔር አምላክ ከነቢዩ መልእክተኛነት ይልቅ ለነቢዩ የህይወት ጥሪት ግድ ይለዋል፡፡ መልእክተኛው የተበላሸ ከሆነ እንደምን መልእክቱ ንጹህ ሊሆን ይችላል?

አንባቢ ሆይ በዚህ ጉዳይ አስብ! መልእክተኛው አስቀድሞ መስተካከል፣ መታረም፣ መለወጥ የለበትምን?



## ምዕራፍ ስምንት

### የነቢያት የጥሪ መለያዎች

1. የመንፈስ ቅዱስ ኃይል

ነቢያት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተሞሉ መሆን አለባቸው:: የእግዚአብሔር ነቢይ ያለ እግዚአብሔር መንፈስ ከሰዋዊ ማንነቱ በስተቀር ምንም ነው:: በነቢያት ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ መኖር እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ ይመክረናል::

*በነቢያትህም እጅ በመንፈስህ መሰከርህባቸው (ነህ 9:30) ::*

*የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ነቢያት ቢሆኑ፣ በእነርሱ ላይ መንፈሱን ቢያወርድ... (ዘኁ 1129)::*

*አባቱ ዘካርያስም መንፈስ ቅዱስ ሞላበትና ትንቢት ተናገረ (ሉቃ 1:67) ::*

ክርስቲያን ነቢይ ያለ እግዚአብሔር መንፈስ በራሱ ኃይል የለውም:: የሚያደርገው ነቢያዊ ተግባራት ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የታገዙ ናቸው:: ይህንን እውነት የሳተ ነቢይ ሁሉ ፍጻሜው ውድቀትና ውርደት ነው:: ከዚህ እውነት በመነሳት የዘመናችን ነቢያት የእግዚአብሔርን መንፈስ ድል ሳለው አገልግሎታቸው መሻት ይጠበቅባቸዋል::

ነቢዩ ኢሳያስ ነቢያትን የእስራኤል ዓይን ሲል ይጠራቸዋል (ኢሳ 29:10) :: ነቢያት ዓይን መሆን የሚችሉት የእግዚአብሔር መንፈስ ሲኖርባቸው ብቻ ነው:: ከእግዚአብሔር መንፈስ የተነሳ ጥልቅ ሚስጥራትን በውስጥ ዓይናቸው አጥርተው ማየት ይችላሉና::

2. ፍጹም ታዛዥነት

ነቢይ ራሱን ፈጽሞ ለእግዚአብሔር ያስገዛል:: በነቢይነት ሥፍራ የቆመ የአዲስ ኪዳን አገልጋይ ከማንም ይልቅ ራሱን በቅድስና ህይወት ለእግዚአብሔር ያውላል:: በ1ኛ

ነገሥት ምዕራፍ 13 ላይ በመልካም ጀምሮ በውርደት ስለፈጸመ አንድ ወጣት ነቢይ ያወጋናል። የዚህ ነቢይ የውድቀት መንስኤ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ አሻፈረኝ በማለቱ ነበር።

> በማዕድም ተቀምጠው ሳሉ የእግዚአብሔር ቃል ወደ መለሰው ነቢይ መጣ። ከይሁዳም ወደ መጣው ወደ እግዚአብሔር ሰው እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። በእግዚአብሔር አፍ ላይ ዐምፀሃልና አምላክህም እግዚአብሔርን ያዘዘህን ትእዛዝ አልጠበቅህምና፤ ተመልሰህም እንጀራ አትብላ፤ ውሃም አትጠጣ ባለህ ሥፍራ እንጀራ በልተሃልና፤ ውሃም ጠጥተሃልና ሬሳህ ወደ አባቶችህ መቃብር አይደርስም ብሎ ጮኸ። እንጀራም ከበላ በኋላ ውሃም ከጠጣ በኋላ አህያውን ጫነለት። ተመልሶም በሄደ ጊዜ በመንገዱ ላይ አንበሳ አገኝቶ ገደለው። ሬሳውም በመንገድ ላይ ተጋድሞ ነበር። አህያውም በእርሱ አጠገብ ቆሞ ነበር። አንበሳውም ደግሞ በሬሳው አጠገብ ቆሞ ነበር (1ኛ ነገ 13፡22-25)።

ነቢዩ በለዓም የሰበከውን መኖር ቢያቅተውም፣ ለእግዚአብሔር መገዛት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በሚገባ የተረዳ ነቢይ ነበር። በአንድ ወቅት እስራኤልን ለመርገም የተገዛው በለዓም «እግዚአብሔር በአፌ የሚያደርገውን ቃል እርሱን እናገራለሁ» ሲል ተደምጧል (ዘኁ 22፡38) ።

ነቢዩ ኤልሳዕ የነበረውን ስኬታማ የግብርና ኑሮ በመተው የኤልያስ ሎሌ በመሆን ለእግዚአብሔር ታዛዥነቱን አስመስክሯል።

> ከእነርሱም ዘንድ ተመልሶ ሁለቱን በሬዎች ወስዶ አረዳቸው። ሥጋቸውንም በበሬዎቹ ዕቃ ቀቀለው። ለሕዝቡም ሰጣቸው፤በሉም። እርሱም ተነስቶ ኤልያስን ተከትሎ ሄደ። ያገለግለውም ነበር (1ኛ ነገሥት 19፡21) ።



### 3. ከእግዚአብሔር ጋር ሠላም መፍጠር

ነቢይ የሆነ አገልጋይ ከእግዚአብሔር ጋር ሠላም ሆኖ ይኖራል። ንግግሩ ከሁኔታዎች የተነሳ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ይስማማል።

አንዳንድ ጊዜ ነቢይ መንገድ ስቶ የስሕተት መንገድ ውስጥ የሚገባበት ጊዜ አለ። በዚያን ጊዜ ብቸኛ አማራጩ ንስሓ ገብቶ ከአምላኩ ጋር ሠላም መፍጠር ብቻ ነው። በአንድ ወቅት ነቢዩ ኤርሚያስ ወደ ንስሓ ህይወት ተመልሶ ከአምላኩ ጋር ሠላም ይፈጥር ዘንድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥሪ ሲደርሰው እናያለን።

> ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ብትመለስ እመልስሃለሁ። በፊቴም ትቆማለህ። የከበረውንም ከተዋረደው ብትለይ እንደ አፌ ትሆናለህ። እነርሱ ወደ አንተ ይመለሳሉ፣ አንተ ግን ወደ እነርሱ አትመለስም። ለዚህ ሕዝብ የተመሸገ የናስ ቅጥር አደርግሃለሁ። ይዋጉሃል። እኔ ግን ለማዳን ከአንተ ጋር ነኝና አያሸንፉህም። ከክፉ ሠዎችም እታደግሃለሁ። ከአመጸኞችም ጡጫ እቤዥሃለሁ (ኤር 15፡19-20) ።

### 4. ትዕግስት ማድረግ

ትዕግስት የነቢያት አንዱ መገለጫ ባህሪይ ነው። እግዚአብሔርን ለመጠበቅ ትዕግስት ያስፈልጋል። እግዚአብሔር የተናገረው ቃል ፍጻሜ ተፈጻሚነት ያገኝ ዘንድ፣ ትዕግስት ወሳኝ የነቢያት ባህሪ መሆን አለበት።

ወደፊት ሲሆን ስላለው ነገር ትዕግስት እንደሚጠይቅ ከትንቢተ ዳንኤል መጽሐፍ እንረዳለን።

> እርሱም እንዲህ አለኝ። ዳንኤል ሆይ ቃሉ እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ የተዘጋና የታተመ ነውና ሂድ (ዳን 12፡9) ።

የእግዚአብሔርን ጊዜ ተሻምቶ አንድን ጉዳይ መፈጸም ህይወትን በመራራ ትግል ውስጥ ለመክተት የሚደረግ ጥረት ነው።

5. ታማኝነትና እውነተኛነት

በመጀመሪያ ደረጃ ነቢይ ታማኝ ለመሆን እውነት ለሆነ ጉዳይ ብቻ ህይወቱን መስጠት ይገባዋል። በዘመናችን ቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ነቢያት በእውነት ላይ የማመቻመች አዝማሚያ ይታይባቸዋል። ዳሩ ግን ነቢይ የእግዚአብሔር አፍ ነው። እግዚአብሔር ደግሞ የእውነት መሰረት ነው። ከእርሱ ዘንድ እውነት ፈልቆ ለህዝቦቹ ይደርሳል። ማድረሻ መንገዱ ነቢያቶቹ ናቸው። በታማኝነት ይህንን እውነት እንዴት ማድረስ እንዳለባቸው ብርቱ ጥንቃቄ ያሻቸዋል።

6. ራስን ዝቅ ማድረግ

ትዕቢት ነቢያትን ለሞት ይዳርጋቸዋል። ነቢያት በትዕቢት መረብ እንዳይጠላለፉ፣ እግዚአብሔር አምላክ በእሳት ውስጥ የሚያሳልፋቸው በዚህ ምክንያት ነው። በአገራችን ውስጥ ነቢያት ፈልቀው መልካም ተስፋ እየታየ ቢሆንም፣ ብዙዎች በትዕቢት ቋራ ውስጥ ገብተው እናገኛቸዋለን። ሐዋሪያው ጳውሎስ በምድረ ቆሮንቶስ ላሉ ቅዱሳን በላከው ደብዳቤ ነቢያት በትንቢት አገልግሎታቸው በትዕቢት እንዳይወድቁ ይህንን ማስጠንቀቂያ አዘል ቃል ጽፎላቸዋል።

> ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም። ትንቢት ቢሆን ይሻራል። ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ። እውቀትም ቢሆን ይሻራል። ከእውቀት ከፍለን እናውቃለንና። ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለንና (1ኛ ቆሮ 13:8-10) ።

በትዕቢት መንፈስ በነቢያት ቢሮ ተቀምጦ ማገልገል አይቻልም። ፓውል ሳንፎርድ የኤልያስ ተግባር በሚለው መጽሐፍ ‹‹ነቢያት ራሳቸውን ፈጽሞ ዝቅ ማድረግ



ሲጀምሩ ያን ጊዜ በነቢያት ተግባራቸው በእርግጥም መለማራት ይችላሉ›› ይላል። ራስን ከፍ ማድረግና የራስን ክብር መፈለግ የነቢያትን አገልግሎት በአጭር ያስቀራል።

7. ርህራሄ

ብዙ ጊዜ የብሉይ ዘመን ነቢያት ጨካኝና ማመቻመች የማያውቁ ተደርገው ይቀርባሉ። እርግጥ ነው በእውነት ላይ ማመቻመች አያውቁም ነበር። ዳሩ ግን ጨካኞች አልነበሩም። በዘመናቸው ከነበሩት ነገስታትና ካህናት ይልቅ እምባቸውን በርህራሄ መንፈስ በየጊዜው ስለ ሠዎች ያነቡ ነበር። ለምሳሌ ነቢዩ ኤርሚያስ እግዚአብሔር አምላክ ጫን ያለ መልእክት ለህዝቡ እንዲያደርስ ሲልከው ቁጭ ብሎ ያነባ እንደነበር ከመጽሐፉ እንረዳለን።

> በሕዝቤ ሴት ልጅ ስብራት እኔ ተሰብሬያለሁ፤ ጠቁሬማለሁ... (ኤር 8:2)።

> ተወግተው ስለሞቱ ስለ ሕዝቤ ሴት ልጅ ለዊ ሌሊትና ቀን አለቅስ ዘንድ ራሴ ውሃ፣ዓይኔም የእምባ ምንጭ በሆነልኝ (ኤር 9:1) ።

በተለምዶ ነቢዩ ኤርሚያስ ‹‹አልቃሻው ነቢይ›› ተብሎ ይጠራል። የልቅሶው መሰረት ህዝቡን ስለሚወድና የእግዚአብሔርን መንገድ መሳት የሚያመጣውን ብርቱ ቅጣት ምን እንደሆነ አስቀድሞ ይሰማው ስለ ነበር ነው።

ኤርሚያስ በጉድጓድ ተጥሎ ስለ ራሱ ሲያለቅስ አናገኘውም። ይልቁንም ልቡ በሀዘን ስሜት ተገድቶ ያለቅስ የነበረው በህዝቡ ላይ ሊመጣ ስላለው የመከራ ገጽታ ነበር እንጂ።

8. ድፍረትና ብርታት

ከእግዚአብሔር ዘንድ እውነተኛ ጥሪ ያላቸው ነቢያት ፍጹም ድፍረትና ብርታት በሁሉ ዙሪያ ያሳያሉ፡፡ በርካታ ነቢያት በንጉሰታትና የፖለቲካ መሪዎች ፊት በድፍረት ቀርበው እውነትን በአደባባይ ያወራሉ፡፡ ስለ እውነትም ሲሉ ይሰዋሉ፡፡

> እንዲህም አለኝ፡፡ የሰው ልጅ ሆይ ተነሥተህ ወደ እስራኤል ቤት ሂድ፡፡ ቃሌንም ተናገራቸው፡፡ ወደ እስራኤል ቤት እንጂ ንግግራቸው ወደ ጠለቀው፣ ቋንቋቸውም ወደ ማይታወቅ ሕዝብ አልተላክህምና፡፡ ንግግራቸው ወደ ጠለቀው፣ ቃላቸውንም ታውቅ ዘንድ ወደ ማይቻልህ ሕዝብ አላኩህም፡፡ ወደ እነዚያስ ልኬህ ቢሆን ኖሮ በሰሙህ ነበር፡፡ ነገር ግን የእስራኤል ቤት ሁሉ የጠነከረ ግምባርና የደነደነ ልብ አላቸውና እኔንም መስማት እምቢ ብለዋልና፡፡ የእስራኤል ቤት አንተን አይሰሙህም፡፡ እነሆ ፊትህን በፊታቸው፣ ግምባርህንም በግምባራቸው አጠንክሬያለሁ፡፡ ከቡላድ ድንጋይ ይልቅ እንደ አልማዝ ግንባርህን አጠንክሬያለሁ፡፡ እነርሱ ዓመጸኛ ቤት ቢሆኑ አትፍራቸው፡፡ ከፊታቸውም የተነሳ አትደንግጥ (ሕዝ 3:4-9) ፡፡

እንደ ነቢዩ ሕዝቅኤል የነቢይነትን ተግባር ለመወጣት ከባድ ድፍረት ይጠይቃል፡፡ በተለይ በዚህ ዘመን ቤተክርስቲያን ከዋና ራሷ ከክርስቶስ ተለይታ በአመጽ መንገድ ስትገኝ፣ እርሷን ወደ ቀናው መንገድ ለመመለስ መለኮታዊ የድፍረት ፀጋ ነቢያት ያሻቸዋል፡፡

እውነተኛ ነቢያት ከድፍረታቸው የተነሳ እንደ እብድ የሚቆጠሩበትም ጊዜ ይኖራል፡፡ ከፊት ለፊታቸው የሞትና ጽዋ እንኳን ተዘጋጅቶ በድፍረት ሲጠጡት ዝግጁዎች ናቸው፡፡ ዳሩ ግን እውነተኛ ነቢያት በድፍረታቸው አደጋ ውስጥ እንዳይገቡ ራሱ እግዚአብሔር አምላክ ስለ እነርሱ ይሟገታል፡፡



> የቀባኋቸውን አትዳስሱ፡፡ በነቢያቴም ክፉ አታድርጉ፡፡ ሰው ክፉ ያደርግባቸው ዘንድ አልፈቀደም፡፡ ስለ እነርሱ ነገስታትን ገሰጸ፡፡ (1ኛ ዜና 16፡ 21-22) ፡፡
>
> የቀባኋቸውን አትዳስሱ፡፡ በነቢያም ክፉ አታድርጉ ብሎ ሰው ግፍ ያደርግባቸው ዘንድ አልፈቀደም (መዝ 105:14-15) ፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## የነቢያት ዋና ዋና ሚና

ነቢይ የእግዚአብሔር አፍ ነው፡፡ ነቢይ ይገስጻል፣ ያስጠንቅቃል፣ አቅጣጫ ይሰጣል፣ ያበረታል፣ ያስተምራል፣ ይመክራል፣ የእግዚአብሔርን ቃል ወደ ሕዝቦች ያደርሳል፡፡ ምላሽም ከሕዝቡ ይቀበላል፡፡

ነቢያት ምክራቸው ከሰራዊት ጌታ ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ነው፡፡ ሀሰተኞችን በሩቅ ሆነው ይፋለማሉ እንጂ በምክራቸው ውስጥ አይሳተፉም፡፡ ‹‹ቃሉን ያጸና ዘንድ በእግዚአብሔር ምክር የቆመ ማን ነውና? ቃሉንስ ያደመጠ የሰማስ ማን ነው? ›› (ኤር 28:18) ፡፡

ነቢያት ከእግዚአብሔር የሆነን ልዩ ልዩ ሀሳብ እንደ እርሱ ሆነው ለሌሎች ያሰማሉ፡፡ ነቢያት በተለምዶ በሚታወቁበት የትንቢት አገልግሎት ብቻ የተወሰኑ አይደሉም፡፡ በተለይም በእኛ አገር እንደምናየው ትንቢት በመናገር ላይ ብቻ አገልግሎታቸው ተወስኖ አይቀርም፡፡ እውነተኛ ነቢያቶች የአገልግሎት ጥሪያቸው ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ በሁሉም የክርስትና ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ዕድገት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ናቸው፡፡

1. የነቢያት የጸሎት አገልግሎት

ጸሎት የነቢያት ዋና የአገልግሎት መስክ ነው፡፡ አንድ ነቢይ የእግዚአብሔርን ልብ በጸሎት ትጋት ይታወቃል፡፡ ከሚያደርገው የዘወትር ጸሎት የተነሳ፣ ሠማያዊው ዓለም በምድር ላይ ምን እያደረገ እንደሆነ ጥልቅ ግንዛቤ ያገኛል፡፡ ‹‹ኢየሩሳሌም ሆይ ጉበኞችን በቅጥርሽ ላይ አቁሚያለሁ፣ ቀንና ሌሊት ከቶ ዝም አይሉም›› (ኢሳ 62፡6-7) ፡፡

ጸሎት የነቢያት የአገልግሎት ዓይል ሰዉ ምግብ ነው፡፡ በጸሎት አማካኝነት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለውን ሰፊ ክፍተት ያጠብባሉ፡፡ በዚህ ጥሪ ምሳሌ የሚሆነን ሙሴ ነው፡፡ ሙሴ እግዚአብሔር በህዝቡ ላይ በሚቆጣ ጊዜ የአማላጅነቱን ሚና በብርቱ ይወጣ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይተርክልናል፡፡



የአንድ ነቢይ መልዕክት የሚወሰደው በእግዚአብሔር ፊት በሚያደርገው የጸሎት ቆይታ ነው፡፡ በጸሎት ሥፍራ በሚያደርገው ቆይታ የእግዚብሔር ወቅታዊ የልብ ትርታ ይሰማዋል፡፡ ከዚህ የተነሳ ነቢይ በጸሎት ቆይታ ከእግዚአብሔር ዘንድ ቃል ተቀብሎ ለህዝቡ ያስተላልፋል፡፡

2. መከራን መቀበል

ነቢያት መከራን ለመቀበል የተጠሩ አገልጋዮችም ናቸው፡፡ በህዝቦች ላይ የሚደርስ መከራ ምን እንደሚመስል ስሜቱ አስቀድሞ በእነርሱ ህይወት ያልፋል፡፡ በእነርሱ ላይ ከሚደርሰው መከራ የተነሳ ሰዋዊ ማንነታቸውን በሚገባ ይገነዘባሉ (ኤር 20፡7-10) ፡፡ ከዛም ባሻገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ከበድ ብሎ የሚመጣውን የትንቢት ድምጽ ርህራሄ በሞላበት የፍቅር መንፈስ ሆነው ለሌሎች ያስተላልፋሉ፡፡ በነህሚያ ውስጥ ያለፈው መከራም ፋይዳው ይኸው ነበር ፡፡

> በእግዚአብሔር ቤት የተሾመው አለቃ የካህኑ የኢሜር ልጅ ጳስኮር ኤርሚያስ በዚህ ነገር ትንቢት ሲናገር ሰማ፡፡ ጳስኮርም ነቢዩን ኤርሚያስን መታው፡፡ በእግዚአብሔርም ቤት በነበረው በላይኛው በብንያም በር ባለው በእግር ግንድ ውስጥ አኖረው (ኤር 20፡1-2) ፡፡

ብዙ ሠዎች በአገራችን ነቢያት ነን ብለው ብቅ እያሉ ነው? በአባቶች ነቢያት የደረሰውን መከራስ ለመቀበል ምን ያህል ዝግጁዎች ናቸው?

3. አምልኮን ማካሄድ

የነቢያት አገልግሎት በቤተክርስቲያን የአምልኮ ሥርዓት ውስጥ ትልቅ ሚና ይጫወታል:: በቤተክርስቲያን የአምልኮ ሥርዓት ውስጥ የነቢያትን ሚና ሐዋሪያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ያስቀምጣል::

> ነቢያትም ሁለት ወይም ሦስት ሆነው ይናገሩ:: ሌሎችም ይለዩአቸው:: በዚያ ለሚቀመጥ ለሌላ ግን አንድ ነገር ቢገለጥለት ፊተኛው ዝም ይበል:: ሁሉም እንዲማሩ ሁሉም እንዲመከሩ ሁላችሁ በእያንዳንዳችሁ ትንቢት ልትናገሩ ትችላላችሁ:: የነቢያትም መንፈስ ለነቢያት ይገዛሉ:: እግዚአብሔር የሠላም አምላክ ነው እንጂ የሁከት አምላክ አይደለምና:: በቅዱሳንም አብያተ ክርስቲያናት እንዲህ ነው (1ኛቆሮ 14:29-33) ::

የእግዚአብሔርን ድንቅና ታላቅነት የሚያውጅ ትንቢታዊ ንባሌ ነፍስን ለአምልኮ ያነሳሳል:: በ1ኛ ዜና 24 ላይ ነቢያት የሙዚቃ መሳሪያ ባለበት ቤተ-መቅደስ ውስጥ ትንቢታዊ የአምልኮ ሥርዓት ያደርጉ እንደነበር ቅዱስ ቃሉ ይመሰክራል:: ይህ አገልግሎት ለዛሬዪቱ ቤተክርስቲያንም እየጠቀመ ይገኛል:: ነቢይቱ ማሪያም የእስራኤል ልጆች ቀይ ባህርን በበረታ የእግዚአብሔር ክንድ ከተሻገሩ በኋላ፣ ቡድኑን በድንቅ የዝማሬ አምልኮ ስትመራ እናገኛታለን::

> የአሮን እህት ነቢይቱ ማሪያምም ከበሮ በእጅዋ ወሰደች:: ሴቶችም ሁሉ በከበሮና በዘፈን ከኋላዋ ወጡ:: ማሪያምም እየዘመረች መለሰችላቸው:: በክብር ከፍ ብሎአልና ለእግዚአብሔር ዘምሩ:: ፈረሱንና ፈረሰኛውንም በባህር ጣለ (ዘፀ 15:20-21) ::

በአንድ ወቅት ንጉሥ ዳዊትም ለአምልኮተ እግዚአብሔር እርሱና የሰራዊቱ አለቆች እነ አሳፍ፣ እነ ኤዶታም በመሰንቆና በጸናጽል ትንቢት የሚናገሩትን ሠዎች ለማገልገል እንደተለዩ የ1ኛ ዜና መዋዕል ምዕራፍ 25:1-6 ክፍል ያስነብበናል::



4. የሚያንጽ ምክር

ቅዱሳንን በምክር አገልግሎት መድረስ የከበረ አገልግሎት ነው:: ይህ ተግባር ቤተክርስቲያን ውስጥ በአብዛኛው በነቢያት ትከሻ ላይ ያርፋል::

> ትንቢትን የሚናገር ግን ለማነጽና ለመምከር ለማጽናናትም ለሰው ይናገራል:: (1ኛ ቆሮ 14:3)

ከነቢያት አንደበት የሚወጣ ቃል ቤተክርስቲያንን በእጅጉ ያንጻል:: በተለይም ደግሞ ቤተክርስቲያን ፈተናና የከፋ መከራ በገጠማት ጊዜ ነቢያት ታላቅ የመጽናናት ቃል ምንጮች ሆነው ይገኛሉ::

መጽሐፍ ቅዱስ በነቢያት አገልግሎት አማካኝነት ለነገስታትና ለህዝቦች ይመጣ የነበረው ቃል የብርታትና የመጽናናት ምክንያት እንደነበር ያስታውቀናል::

> አሳም ይህን ቃልና የነቢዩን የዓዴድን ትንቢት በሰማ ጊዜ ልቡ ጸና:: ከይሁዳና ከብንያምም አገር ሁሉ በተራራማውም በኤፍሬም አገር ከያዛቸው ከተሞች ጸያፉን ነገር አስወገደ:: በእግዚአብሔርም ቤት ፊት የነበረውን የእግዚአብሔርን መሰዊያ አደሰ (1ኛ ዜና 15:8) ::

ተስፋ በቆረጥንባቸው ጊዜያት፣ ሁሉም ሁሉ ጨልሞብን በተገኘበት ሠዓት እግዚአብሔር አምላክ ነቢያቱን ወደ እኛ ልኮ ብዙ ጊዜ አበርትቶናል::

> ነቢያቱ ሐጌና የአዶ ልጅ ዘካሪያስ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ለነበሩ አይሁድ በእስራኤል አምላክ ስም ትንቢት ተናገሩላቸው:: በዚያን ጊዜም የሰላትያል ልጅ ዘሩባቤል የኢዮሴዴቅም ልጅ ኢያሱ ተነስተው በኢየሩሳሌም ያለውን የእግዚአብሔርን ቤት መስራት ጀመሩ:: የሚያግዙአቸውም የእግዚአብሔር ነቢያት ከእነርሱ ጋር ነበሩ (ዕዝ 5:1-2) ::

## 5. የመጪውን ጊዜ መልክ ማሳወቅ

የወደፊቱን ጊዜ አስቀድሞ መናገር አንዱ የነቢያት አገልግሎት ነው፡፡ ሁሉም የብሉይ ዘመን ነቢያት አገልግሎታቸውን የጀመረት በዚህ መንገድ ነበር፡፡ አንድ ነቢይ ከአምላኩ ጋር ያለው ቅርበት በጸሎት እየጨመረ በሄደ ቁጥር፣ መጪው ዘመን ምን መልክ እንዳለው በቀላሉ መረዳት ይችላል፡፡

ነቢያት ወደፊት ሊመጣ ያለውን ጥፋት ለህዝቦቻቸው ተናገረው፣ ለህዝቦቻቸው የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ደውል ያሰማሉ፡፡ እንዲሁም ህዝቦች የዛሬውን መከራቸውን ዘንግተው መጪውን ዘመናቸውን በተስፋ እንዲጠብቁ ነቢያት ይረዷቸዋል፡፡ ከዛም ባሻገር የወደፊቱን ታሪካዊ ሁነት አልፈው በመመልከት ዛሬ ሲሆን ያለውንም ብርቱ ጉዳይ የማወቅ መሰኮታዊ ብቃት አላቸው፡፡

> በዚያም ወራት ሕዝቅያስ እስከ ሞት ድረስ ታመመ፡፡ ነቢዩም የአሞጽ ልጅ ኢሳያስ ወደ እርሱ መጥቶ ‹‹እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡፡ ትሞታለህ እንጂ በህይወት አትኖርምና ቤትህን አስተካክል አለው (2ኛ ነገ 20፡፡1-2) ፡፡

ነቢዩ ኢሳያስ በሕዝቅያስ ላይ ሊመጣ ያለውን ሞት አስቀድሞ በመናገሬ ከሞት አትርፎታል፡፡ ነገ ሊሆን ያለውን ጥፋት በዛሬ ትንቢታዊ ቃል ጥፋትን መመለስ ይቻላል፡፡ ከላይ ያየነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለዚህ ሀሳብ በቂ ማስረጃ ነው፡፡

## 6. ምሪትና አቅጣጫን ማሳየት

ቤተክርስቲያንና ግለሰቦች ግራ በመጋባት ህይወት ውስጥ ቢገኙ፣ ነቢያት ግልፅ ገብተው ካሉበት የህይወት ፈተና የሚወጡበትን አቅጣጫ ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል ነቢዩ ጋድ ንጉስ ዳዊት በከፋ ችግር ውስጥ ሊወድቅ ባለት ጊዜ የመውጫውን መንገድ ሲጠቁመው እናያለን፡፡

> ነቢዩ ጋድም ዳዊትን ተነሥተህ ወደ ይሁዳ ምድር ሂድ እንጂ በአምባው ውስጥ አትቀመጥ አለው፡፡ ዳዊትም ተነስቶ ወደ ሔሬት መጣ (1ኛ ሳሙ 22፡5) ፡፡

በዚህ ጉዳይ አንድ ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚገባ ጉዳይ አለ፡፡ አቅጣጫ ጠቋሚ ትንቢቶች ለግለሰብ በሚመጡበት ጊዜ፣ግለሰቡ ትንቢቱን በሚገባ መርመር አለበት፡፡ እዚህ አገራችን ውስጥ በግለሰብ ነቢይ በተነገሩቸው ትንቢት መሠረት ንብረታቸውን ሸጠው ወደሌላ የህይወት አቅጣጫ ለመግባት ሲሞክሩ ብዙ ሠዎች በኪሳራ ተመተዋል፡፡ አቅጣጫ ጠቋሚ ትንቢት አምጭው ግለሰብ በመጀመሪያ በቤተክርስቲያን የታቀፈና የታመነበት ነቢይ ሲሆን ይገባል፡፡ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለ የትንቢት አገልግሎት መጀመሪያውኑ ለሰማኙ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የተገለጠ ነው፡፡ ከነቢዩ የሚመጣው ትንታቢዊ ቃል ደግሞ ቀድሞ የተነገረን ትንቢት ማጽኛ ቃል ነው፡፡

## 7. ህልምን መፍታትና መተርጎም

ሌላኛው የነቢያት አገልግሎት ህልምን መፍታት መተርጎም እንደሆነ እናያለን፡፡ የእግዚአብሔርን መንፈስ በሚገባ ማዳመጥ ያልቻሉ ቅዱሳን አሉ፡፡ የእግዚብሔርን መንፈስ በሚገባ ማዳመጥ ያልቻሉ ቅዱሳን አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ፍቃዱንና ሀሳቡን በህልም ያሳውቃቸዋል፡፡ ህልምን ከእግዚአብሔር ዘንድ ከመቀበል ሌላ ነቢያቶች በሌላ ሰው የታለመን ህልም የመፍታት ልዩ ብቃት አላቸው፡፡ ዳንኤል ህልምን የመተርጎም ልዩ የጥበብ መንፈስ ነበረበት (ዳን 2፡1-28) ፡፡

ዳንኤል በአንድ ምሽት ንጉስ ናብኩደነጾር የህልም ፍቺ ሲረዳ እንዲህ ሲል ተናገረ፡፡

> ጥበብና ኃይል ለእርሱ ነውና፡፡ የእግዚብሔር ስም ከዘላለም እስከ ዘላለም ይባረክ፡፡ ጊዚያትንና ዘመናትን ይለውጣል፡፡ ነገስታትን ያፈልሳል፡፡ ነገስታትንም ያስነሳል፡፡ ጥበብን ለጠቢባን፣ እውቀትንም ለአስተዋዮች ይሰጣል፡፡ የጠለቀውንና የተሰወረውን ይገልጣል፡፡

> በጨለማ ያለውን ያውቃል፡፡ ብርሃንም ከእርሱ ጋር ነው፡፡ ጥበብንና ኃይልን የሰጠኸኝ፣ እኛም የለመንህን ነገር አሁን ያስታወቅኸኝ፣ አንተ የአባቶቼ አምላክ ሆይ፣ የንጉሡን ነገር አስታውቀኸኛልና እገዛልሃለሁ፡፡ አመሰግንሃለሁ (ዳን 2፡19-23) ፡፡

ሕልም ብዙ ጊዜ ቀጥተኛ ትርጉም ሳይኖረው ይችላል፡፡ የተለያዩ ሠዎችንና ቁሳዊ ነገሮችን በሕልማችን በምሰሳ መልክ እናያቸዋለን፡፡ ለምሳሌ ዮሴፍ ሠማይን፣ ጨረቃንና አስራ አንዱን ከዋክብት ሲሰግዱለት በሕልም አየ፡፡ እነዚህ ቀጥተኛ የሕልም እይታዎቹ በቀጥታ መጥተው ለዮሴፍ እውን አልሆኑም፡፡ ለዮሴፍ የህልሙ ፍቺ የተገለጸው አባቱና አስራ አንዱ ወንድሞቹ መጥተው በግብጽ ምድር ሲሰግዱለት ያን ጊዜ የህልሙ ፍቺ እውን ሆነለት (ዘፍ 37፡5-12) ፡፡

በዘመናችን ያሉ ነገስታትና የአገር ገዢዎች አንድ ብርቱ ህልም የሚያልሙበት ጊዜ አለ፡፡ የህልሙን ትርጓሜ ካላወቁት በቤተክርስቲያን ውስጥ አመኔታ የተጣላባቸው ነቢያች ህልም በመፍታት ሲረዷቸው ይችላል፡፡

8. መገሰጽና ማረም

አንዳንድ ጊዜ የነቢያት አገልግሎት አሉታዊ አንድምታ አለው፡፡ እንደ ኤርሚያስ ያሉ ነቢያት በመትከልና በመንቀል ትንቢታዊ አገልግሎት ላይ ሊሰማሩ ይችላሉ፡፡ በእግዚአብሔር እውነት ላይ ያልተመሠረተን ሥርዓት ሁሉ ገለባብጠው መልክ ባለው ሥርዓት ተክለዋል፡፡ ኤሊያስ በዘመኑ የነበረውን ሥርዓት አልበኝነት የሞላበትን የክፉ አሠራር በጽኑ የተቃወመ ነቢይ እንደሆነ እናያለን፡፡ በዘመናችን ያሉትም ነቢያት በቤተክርስቲያን ላይ ሊመጣ ያለውን ጥፋት ደፍረው መናገር ይጠበቅባቸዋል፡፡

ነቢያት ሁልጊዜ ሲታሰቡ የተግሳጽና የቁጣ መልእክተኞችም እንደሆኑ ማወቅ ጥበብ ነው፡፡ እውነተኛ የሆነ ነቢይ ሲመጣ በህዝብ ላይ የጽድቅ ፍርሃትም ይዞ ይመጣል፡፡ በህዝብ ላይ የሚመጣው ፍርሃትም በነቢያቱ ህይወትም ላይ ዛቻና ቁጣን፣



ነቀፌታንም ሲያመጣ ይችላል፡፡ እንዲሁ ካለው ህይወት የጥንት ነቢያትም አላመለጡም፡፡ በጥፊ ተመተዋል፡፡ በጉድጓድ ውስጥ ተጥለዋል፡፡ በዘመኑ ያሉትም ነቢያት ከዚህ አያመልጡም፡፡ የተመቻቸ የህዝብ ጆሮ አስደሳች የነቢያት ኑሮ በጥያቄ ውስጥ ይገባል፡፡

9. ሊመጣ ያለውን አደጋ ማስታወቅ

ነቢዩ አጋቦስ በሐዋሪያው ጳውሎስ ህይወት ላይ በኢየሩሳሌም ሊመጣ ያለውን መከራ በድርጊት ሲያመላክት እናገኘዋለን (ሐዋ 21፡10-11) ፡፡ እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ህዝቡን በዚህ መንገድ የልብ ፍቃዱን ያስታውቀዋል፡፡ ነቢያት ጉበኞች ናቸው የመባሉ ሚስጥርም ይኸው ነው፡፡ የእግዚአብሔር ህዝብ ሊመጣበት ያለውን መከራ አስታውቀው ከጥፋት ያድኑታል፡፡

> በእውነት ጌታ እግዚአብሔር ሚስጥሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም፡፡ አንበሳ አገሳ የማይፈራ ማነው? (አሞጽ 3፡5-7)፡፡

በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ሊመጣ ያለውን ሁነት አስቀድሞ የማስታወቁ ተግባር በነቢያት ላይ የተጣለ ነው፡፡ ኤሊያስ የእሳት ነቢይ ተብሎ ይታወቃል፡፡ ሊመጣ ያለውን እሳት አስቀድሞ ያስጠነቅቃል፡፡ በምልጃውም የእሳቱን ምጽአት ይገታል ወይም እንዲዘንብ ያደርጋል፡፡

በዘመናችን ያሉ ነቢያትም ዛሬም ይህንን ተግባራቸውን እየተወጡ ይገኛሉ፡፡ ነቢዩ ቲቢ ጆሽዋ በዘመናችን በዚህ አገልግሎቱ ይታወቃል፡፡ ከናይጄሪያ በሚተላለፈው የኢማኑኤል ቲቪ አማካኝነት ሊመጡ ያሉትን የአለማችንን አስከፊ ክስተቶች ተናግሮ ያልተፈጸሙ ትንቢቶች የሉም፡፡

10. የጊዜውን ምልክቶች መተርጎም

11. አይሁዳውያን የአየር ሁኔታቸውን ተረድተው የጊዚያቸውን ምልክት ያውቃሉ። ዳሩ ግን የእግዚአብሔርን ሀሳብ ባለማወቃቸው ጌታ ኢየሱስ በአንድ ወቅት ሲነቀፋቸው እናያለን።

> ደግሞም ሕዝቡን እንዲህ አለ። ደመና ከምዕራብ ሲወጣ ባያችሁ ጊዜ ወዲያው ዝናብ ይመጣል ትላላችሁ። ... እናንተ ግብዞች የምድሪንና የሠማዩን ፊት ልትመረምሩ ታውቃላችሁ። ነገር ግን ይህን ዘመን የማትመረምሩ እንዴት ነው? (ሉቃ 12:54-56)።

ጊዜውን የሚረዳ ነቢይ የጊዜውን ምንነት ይተረጉማል። የጊዜውን አስተሳሰብ በመንፈሳዊ መንጽር አጥርቶ በማየት ለትውልዱ ትንቢታዊ ቃሉን ያስተላልፋል።

12. ትውልድን መሞገት

ነቢይ ትውልድን ይሞግታል። የጥንት ነቢያቶች ነገስታትን በአገራዊ ጉዳይ ሞግተዋቸዋል። ከራሳቸው አገር ነገስታት አልፈውም፣ በሌሎችም አገራትን ነገስታትን ላይ የሙግት ቃላቸውን ሰንዝረዋል (ኢሳ :12፣ ኤር 46:51) ።

የህዝብ መነሳሳት፣ የምድራዊ ነገስታት መውደቅና መነሳት፣ የነገስታቶች ንግስናና ሹመት ውስጥ ሁሉ የነቢያት ቃል በኃይል ይሰራል።

ከዚህም በተጨማሪ ነቢያት በሃጢያት ምክንያት በህዝቦች ላይ ሊመጣ ያለውን ጥፋት ያመለክታሉ።

13. የሥነ-መለኮት ግንዛቤ



ነቢያት ስለ እግዚአብሔር ማንነት በቂ ግንዛቤ አላቸው። የእርሱ መንግስት እንደራሴ በመሆናቸው እርሱን ስለመልከት የሚቀርብ ማናቸውንም ጥያቄዎች ተቀብለው ምላሽ ይሰጣሉ።

14. በሽታን መፈወስ

ነቢያት የፈውስ መልእክተኞችም ናቸው። ከነቢያት መካከል ነቢዩ ኤልሳዕ በዚህ አገልግሎቱ ይታወቃል።

> ኤልሳዕም ወደ ቤት በገባ ጊዜ ህጻኑ እነሆ ሞቶ በአልጋው ላይ ተጋድሞ ነበር። ገብቶም ከሁለቱ በኋላ ዘጋ። ወደ እግዚአብሔርም ጸለየ። መጥቶም በህጻኑ ላይ ተኛ። አፉንም በአፉ፣ ዓይኑንም በዓይኑ እጁንም በእጁ ላይ አድርጎ ተጋደመበት። የህጻኑም ገላ ሞቀ። ተመልሶም በቤቱ ውስጥ አንድ ጊዜ ወዲህ ወዲያ ተመላለሰ። ደግሞም ወጥቶ ሰባት ጊዜ በህጻኑ ላይ ተጋደመ። ህጻኑም ዓይኖቹን ከፈተ። (2ኛ ነገ 4:32-35) ።

15. ሌሎችን መሾምና መቀባት

በብሉይ ኪዳን ዘመን ነቢያት ነገሥታትን ይቀቡና ያነግሱ ነበር። ለምሳሌ ሳሙኤል ሳዖልንና ዳዊትን ለንግስና ቀብቷል። ከንጉስ ዳዊት በኋላ የነገሰው ሰለሞንም የተቀባው በእርሱ ነበር።

> ካህኑም ሳዶቅና ነቢዩ ናታን የዮዳሄም ልጅ በናያስ ከሊታውያንና ፈሊታውያንም ወረዱ። ሰለሞንም በንጉሥ በቅሎ ላይ አስቀምጠው ወደ ግዮን አመጡት። ካህኑም ሳዶቅ ከድንኳን የቀባትን ቀንድ ወስዶ ሰለሞንን ቀባ። ቀንደ መለከትም ነፉ። ሕዝቡም ሁሉ እሱን ተከትለው ወጡ። ሕዝቡም ዘፈን ይዘፍኑ

ነበር፡፡ በታላቅም ደስታ ደስ አላቸው፡፡ ከጩኸታቸውም የተነሳ ምድ ተናወጠች (1ኛ ነገ 1:38-39) ፡፡

እግዚአብሔርም አለው (ለኤልያስ) ሂድ በመጣህትም መንገድ በምድረ በዳ ወደ ደማስቆ ተመለስ፡፡ ከዚያም በደረስህ ጊዜ በሶሪያ ላይ ንጉሥ ይን ዘንድ አዛሄልን ቀባው፡፡ በእስራኤልም ላይ ንጉስ ይሆን ዘንድ የናሚስን ልጅ እዩን ቀባው፡፡ በፋንታህም ነቢይ ይሆን ዘንድ የአቤልምሖላን ሰው የሳፋጥን ልጅ ሊዩን ቀባው (1ኛ ነገ 19:13-16) ፡፡

## 16. ነገስታትንና የፖለቲካ መሪዎችን ማማከር

ነቢያት ነገስታትንና የፖለቲካ መሪዎችን የማማከር ሚና ይጫወታሉ፡፡ እግዚአብሔር ለነገሥታት ምሪትን መስጠት ሲፈልግ ነቢያትን ወደ እነርሱ ይልካል፡፡ ንጉስ ዳዊት ለምሳሌ አማካሪዎቹ ናታንና ጋድ የሚባሉ ነቢያት ነበሩ፡፡ ንጉሱ ወሳኝ የአመራር ምሪቶች ባስፈለገው ጊዜ አካሄድን ከእነርሱ ተቀብሉ ይንቀሳቀስ ነበር፡፡

እንዲህም ሆነ ንጉሡ በቤቱ በተቀመጠ ጊዜ እግዚአብሔርም በዙሪያው ካሉት ጠላቶቹ ሁሉ ባሳረፈው ጊዜ ንጉሱ ነቢዩ ናታንን እኔ ከዝግባ በተሰራ ቤት ተቀምጫያለሁ፡፡ የእግዚአብሔር ታቦት ግን በመጋረጃዎች ውስጥ እንደ ተቀመጠ እይ አለው፡፡ ናታንም ንጉሡን እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ሂድ በልብህም ያለውን ሁሉ አድርግ አለው (2ኛ ሳሙ 7:1-4) ፡፡

ነቢዩ ጋድም ዳዊትን ተነሥተህ ወደ ይሁዳ ምድ ሂድ እንጂ በአምባው ውስጥ አትቀመጥ አለው (1ኛ ሳሙ 22:5) ፡፡

በአንድ ወቅት እስራኤላውያን በነቢዩ ኤልሳዕ ምሪት በጠላቶቻቸው መንደር ነውጥና መደናገጥን ፈጥረዋል፡፡



የእግዚአብሔር ሰው ሶሪያውን በዚያ ተደብቀዋልና በዚያ ምፍራ እንዳታልፍ ተጠንቀቅ ብሉ ወደ እስራኤል ንጉስ ላከ፡፡ የእስራኤልም ንጉስ የእግዚአብሔር ሰው ወደ ነገረው ስፍራ ሰደደ፡፡ አንድ ጊዜም ሳይሆን ሁለት ጊዜም ሳይሆን በዚያ ራሱን አዳነ፡፡ የሶሪያም ንጉሥ ልብ ስለዚህ እጅግ ታወከ፡፡ ባሪያዎቹንም ጠርቶ ከእኛ ዘንድ ከእስራኤል ንጉስ ጋር የተወዳጀ እንዳለ አትነግሩኝምን? አላቸው፡፡ ከባሪያዎቹም አንዱ ጌታዬ ሆይ እንዲህ አኮ አይደለም፡፡ ነገር ግን በእልፍኝህ ውስጥ ሆነህ የምትናገረውን በእስራኤል ዘንድ ያለ ነቢይ ኤልሳዕ ለእስራኤል ንጉሥ ይነግረዋል አለ፡፡ እርሱም ልኬ አስይዘው ዘንድ ሄዳችሁ ወዴት እንደሆነ እዩ አለ (2ኛ ነገ 6:9-12) ፡፡

## 17. ታሪክን ማወቅና መረዳት

ነቢያት የታሪክ አዋቂዎችም ናቸው፡፡ ያለፈውም የታሪክ ሁነት አጢነው ቀጣዩን የታሪክ ገጽታ ለተውልዳቸው ያስተላልፋሉ፡፡ አብዛኛውን የብሉይ ታሪኮችን የጻፉት ነቢያቶች እንደሆኑ እናያለን፡፡

የቀረውንም የፊተኛውና የኋለኛውን የዖዝያንን ነገር ነቢዩ የአሞጽ ልጅ ኢሳያስ ጽፎታል 2ኛ ዜና 26:22) ፡፡

የንጉሡም የዳዊት የፊተኛውና የኋለኛው ነገር እነሆ በባለ ራእዩ በሳሙኤል ታሪክ፣ በነቢዩም በናታን ታሪክ፣ በባለ ራእዩም በጋድ ታሪክ ተጽፏል 2ኛ ዜና 29:29) ፡፡

# ምዕራፍ አስር

## የነቢያት የድካም ጎኖች

እግዚአብሔር በነቢዩ ላስቀመጠው ቃል ግድ እንደሚለኝ ሁሉ ስለራሱ ነቢዩም ባህሪዩና ህይወት ግድ ይለዋል:: እግዚአብሔር ነቢያቱ ጥርት ያለ ባህሪይ ተላብሰው በውስጣቸው ያስቀመጠውን መልእክት ለህዝቡ ማድረስ ይፈልጋል::

ነቢያት ብዙ ጊዜ ህይወታቸው የጠራ ሆኖ እንዳይመላለሱ የሚያደርጓቸው በርካታ እንቅፋቶች አሉ:: እነዚህ የነቢያት የእድገት ፀሮች ከነቢያቱ ካልተወገዱ በቀር ነቢያቱ መድረስ ከሚገባቸው የህይወት ምዕራፍ ለመድረስ ይቸግራቸዋል::

### 1. መደናገጥና መፈራነት

ነቢያት በሰው ዘንድ ያላቸውን ተቀባይነት በአንድ ጊዜ የሚያጡበት አንድ የታሪክ አጋጣሚ አለ:: ከተናገሩት የእውነት መልእክት አንጻር በሰሚዎቻቸው ዘንድ ቅሬታ ፈጥሮ፣ ጥላቻና መገለል ይደርስባቸዋል:: ይህ አሉታዊ ተጽእኖ እየበረታባቸው ሄዶ በሥነ-ልቦናቸው ላይ የመፈርነትና የመደናገጥ ስሜት ይነግስባቸዋል:: ይህንን ስሜቶች በልቦናቸው ውስጥ አሳድረው ሳለ እግዚአብሔር እንደገና ሌላ የእውነት መልእክት አስታጥቋቸው ወደ ህዝቡ ይልካቸዋል:: እዚህ ጋ ልብ በሉ! አስቀድሞ በልባቸው ውስጥ ያደገው መፈርነት አሁን እግዚአብሔር አምላክ አስታጥቆ ከላካቸው መልእክት ጋር ተዳምሮ እንዴት ያለ ድብልቅ መልእክት ለህዝብ እንደሚያደርሱ ልብ በሉ! በዚህ ሁኔታቸው እግዚአብሔር ለህዝቡ የፍቅር መልእክት ማስተላለፍ ሲፈልግ፣ እነርሱ ግን ካለፉበት መራር የህይወት ተሞክሮ የተነሳ፣ ድምፀታቸው ሳይቀር ዋናው የእግዚአብሔር መልእክት ላይ የስሜት መደባለቅ መፍጠሩ አይቀሬ ነው::

የመደናገጥና የመፈርነት ስሜት የነቢያት ቀንደኛ ጠላት ነው:: መፈርነት በአገልግሎታቸው ላይ ጥቁር ጥላሸት ይቀባል:: አገልግሎታቸውን እንዲጠየፉት ግፊት



ያደርግባቸዋል:: ይህንን ስሜት ከውስጣቸው ፈንቅሉ ማውጫው መንገድ በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት መቆየትና ኃይል መቀበል ብቻ ነው::

ነቢያት በውስጣቸው ማቆጥቆጥ የጀመረውን መፈርነት በጊዜ ጠራርገው ካላጠፉ፣ የእግዚአብሔር እውነት እየተሸረሸረ መጥቶ ለስህተት አስተምሮቶች እየተጋለጡ ይመጣሉ::

### 2. የኩራት ስሜት

አንዳንድ ነቢያት ኑሯቸው በጽድቅ የተሞላ ነው:: ኃጢያትን ፈጽመው ይጸየፉታል:: ከዚህ የተነሳ አልፎ አልፎ የፈሪሳውያን ስሜት ይደባለቅባቸዋል:: ጽድቅ በበዛበት ማንነታቸው ውስጥ ሃጢያትን በሌላው ሰው ህይወት ውስጥ ሲመለከቱ እጅግ ይጠየፋሉ:: ኩነኔም ያበዛሉ:: የዚህ ምክንያቱ በድካም ህይወት ውስጥ ሳያልፉ በመቆየታቸው ነው:: እግዚአብሔር ለዚህም ነቢያቱን አልፎ አልፎ እጅግ ድካም በበዛበት ህይወት ውስጥ አሳልፎ ዳግም ህይወት የሚዘራባቸው:: ያን ጊዜ ለሌላው ማዘን ይጀምራሉ:: በሃጢያት ወድቆ መገኘት ማለት ምን ማለት እንደሆነም ይረዳሉ:: ፈጥነውም በሃጢያት ጭቃ ውስጥ የተለወሰን ሰው ሲያዩ በፍቅር አጥበውት ለእውነተኛ ንስዓ ያበቁታል::

የኩራት ስሜት የነቢያት አውዳሚ የጦር መሳሪያ ነው:: መዝሙረኛው ዳዊት ሲናገር ‹‹በከንቱ የሚመኩ በዓይኖችህ ፊት አይኖሩም ›› ይላል (መዝ 5:5) ::

በነቢያት አገልግሎት ሌላኛው የኩራት ስሜት ምክንያት የ‹‹እኔነት›› ስሜት ነው:: ይህ የእኔነት ስሜት በአገራችን ውስጥ ባሉ ነቢያት ዘንድ ይሰማል፣ይንጸባረቃልም:: ‹‹እኔ የምናገረው የትንቢት ቃል መሬት ጠብ አይልም›› የሚል ድምጽ ያስተጋባሉ:: እንዲህ ያለ ንግግር ክርስቲያናዊ ድምፀት የለውም:: ይልቁንም ራስን የማጽደስ ተልእኮ እንጂ::

ልሰግድለትም በእግሩ ፊት ተደፋሁ። እርሱም ‹‹እንዳታደርገው ተጠንቀቅ ከአንተ ጋር የኢየሱስም ምስክር ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ። ለእግዚአብሔር ስገድ። የኢየሱስ ምስክር የትንቢት መንፈስ ነውና (ራእ 19፡10) ።

3. ራስን መግስተር

ነቢያቶች አንዱ መገለጫቸው ትሁትናቸው ነው። በዚህ ዘመን እያየን ያለነው ግን ከትህትና ይልቅ ራስን በአንደኛነት ማሀረግ ማማ ላይ ማስቀመጥ ነው። ዳሩ ግን የነቢይነት ጥሪ እግዚአብሔርን ከፍ ማድረግና ስለ ሰዱ ስለ ኢየሱስ ሰብ መተረክ ነው።

በዚህ ዘመን ያሉ ነቢያቶች የራሳቸውን የስም ባንዲራ ከሰቀሉበት አውርደው የአምላካቸውን ስም ከፍ ከፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በመዲናችን እንደምናየው በትላልቅ ፖስተሮች ላይ በንጉስ ወንበር ላይ ተቀምጠው ፎቶ ከመነሳት ይልቅ ኢየሱሳዊ የሆነ አንዳችን ትንቢታዊ ምስል መስቀል ይገባቸዋል።

4. አማጺነት

ኩራት አንዳንድ ጊዜ ወደ አመጽ ተግባር ይመራል። አመጽ ደግሞ የነቢያት የሽባነት ወጥመድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አመጽን ከሟርት ጋር ያመሳስለዋል።

> ዓመጸኛነት እንደ ምዋርተኛ ኃጢያት፣እልከኝነትም ጣዖትንና ተራፊምን እንደ ማምለክ ነው (1ኛ ሳሙ 15፡23) ።



ነቢያት ካላቸው ድንቅ የጸጋ አገልግሎት የተነሳ ዝነኝነትና ታዋቂነት ዱካቸውን እየተከተለ ይመጣል። ምዕመናን በእነርሱ ላይ የሚነሳን አካል በተባበረ ክንድ ይቃወማሉ። ነቢያትም ከኋላቸው የሚከተለውን ህዝብ በመተማመን ጥፋት ውስጥ የሚገቡበት ጊዜ አለ። ለዚህም ነው በምድራችን ያሉ ነቢያት ቤተክርስቲያናቸውን ከፍለው ሌላ ቤተክርስቲያን የመክፈት ብቃታቸው እየጨመረ የመጣው። ዳሩ ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ለቤተክርስቲያን የተሰጣቸውን ጸጋ ለለአግባብ ለግል ምኞት ማስፈጸሚያ ማዋል ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ አደራረግ እንደሆነ ማስተዋል ይጠበቅባቸዋል።

> የሥጋ ስራም የተገለጠ ነው። እርሱም ...ሟርት፣ ጥል፣ክርክር፣ቅንዓት፣ ቁጣ፣አድመኛነት ...የሚመስል ነው (ገላ 5፡20) ።

5. ዝሙት

ጆን ፓውል ጃክሰን ነቢያት ጠላታቸው ከሆነው የፍትወት ፈተና አብዝተው እንዲርቁ ይመክራል። ብዙ የወንጌል ሠዎች በዝሙት ኃጢያት እንደማንኛውም ሰው የመውደቅ ዝንባሌ አላቸው። ዳሩ ግን ነቢያት ከታሪክና ከወቅታዊ ሁነቶች እንደታየት ለዝሙት ኃጢያት በቀላሉ የተጋለጡ ናቸው። ለዚህም ዋንኛ ምክንያቱ ነቢያት በመናፍስት ዓለም ውስጥ ያን መልካም እንቅስቃሴን በመንፈሳቸው የማወቅ ብቃት እንዳላቸው ሁሉ ክፉ የሆኑ መናፍስታዊ እንቅስቃሴዎችንም በመንፈስ ይረዳሉ። በሌላ አነጋገር ነቢያት የእግዚአብሔርን መገኘት እንደሚሰማቸው ሁሉ የሰይጣንንም መገኘት ያውቃሉ። ለምሳሌ አንዲት ችግር የገጠማት እህት ወደ አንድ ነቢይ ቀርባ፣ ነቢዩ የልቧን ሀሳብ በመንፈስ ተረድቶ እንደሚነግራት፣ ለነቢዩ ያላትንም ፍላጎት ነቢዩ ይረዳል። የግድ ሴቲቱ ፍላጎቷን በዓይን ጥቅሻ መግለጥ የለባትም። ነቢዩ የልብ ትርታዋን ይረዳል። በጌታ ኃይል ካልበረታ በቀር ወደ ወጥመዱም ይገባል። በዚህ መንገድ የክፉ ዓለም መናፍስት የቤተክርስቲያን ዓይን የሆኑትን ነቢያትን በዝሙት ወረርሽኝ ለማጥፋት የዘወትር ተጋድሏቸው ነው።

ነቢያት በዝሙት ዓጢያት የሚወድቁበት ሁለተኛው ምክንያት ከስለምና ከቤተክርስቲያን ዘንድ ዘወትር የሚደርስባቸው ማግለልና ተቃውሞ ነው። ይህ ተግዳሮታቸው የብቸኝነትን ሥሜት ይፈጥርባቸዋል። ሰው ሲያሻቸው፣ ሰው ይርቃቸዋል። ያን ጊዜ ከክፉው ዓለም የሚሳቡ ሥጋ ለበስ ተቃራኒ ጾታዎች ወደ መሰሰው ቀርበው የነቢያቱን ህይወት በዝሙት ያረክሳሉ።

6. የሌላውን አጢያት በአደባባይ ማጋለጥ

ነቢያት አንዳንድ ጊዜ የሰውን ሃጢያት ያለ እግዚአብሔር ምሪት በአደባባይ ማውገዝ ይቀናቸዋል። ይህ አካሄድ በግለሰቡ ላይ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ብሎም ሥነ-ልቦናዊ ጉዳት ሊያስከትልበት ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ በደል ፈጻሚውን ግለሰብ በምን መንገድ ቀርበን ከጥፋት መንገድ መመለስ እንዳለብን በማቴዎስ ወንጌል ላይ ጥቆማ ይሰጠናል።

> ወንድምህም ቢበድልህ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ውቀሰው። ቢሰማህ ወንድምህን ገንዘብ አድርገሃል። ባይሰማ ግን ሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነገር ሁሉ እንዲጸና ዳግመኛ አንድ ወይም ሁለት ከአንተ ጋር ውሰድ። እነርሱንም ባይሰማ ለቤተክርስቲያን ንገራት። ደግሞም ቤተክርስቲያንን ባይሰማት እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ (ማቴ 18:15-17) ።

7. ገንዘብን መውደድ

ገንዘብ ነቢያትን የሚያሳውርበትም አጋጣሚ አለ። ነቢያት በገንዘብ ለሚደግፏቸው ሰዎች በቃላቸው የማወደስና የማባባል ድምጸት ከተሰማ ያን ጊዜ ዋና ተልእኳቸውን ዘነጉ ማለት ነው። ነቢያት ትንቢታዊ ቃላቸው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዲያመጣ ቢቻላቸው የገቢ ምንጫቸው ነጻ ከሆነ ሥፍራ ቢሆን ይመረጣል። የቁስና የገንዘብ ፍቅር ለነቢያት የጥፋት በሮች ናቸው። ውስጣቸው በተቀመጠው እውነት ላይ የሀሰት ድሬት ያለብሳሉ።



> እግዚአብሔር ሕዝቤን ስለሚያስቱ ነቢያት እንዲህ ይላል። በጥርሳቸው ሲነክሱ በሰላም ይሰብካሉ። በአፋቸው ግን አንዳች በማይሰጥ ሰው ላይ ሰልፍን ያስቡበታል (ሚክ 3:5) ።

8. ሰውን የማስደሰት ፍላጎት

በአገልግሎት ሰውን ለማስደሰት መሞከር ብርቱ የመጥፊያ መርዝን ለራስ እንደ መቀመም ነው። የሰውን ፍላጎት ያማከለ አገልግሎት ማገልገል በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ በደል ነው።

> ሰውን ወይስ እግዚአብሔርን አሁን እሺ አሰኛለሁን? ወይም ሰውን ደስ ላሰኝ እፈልጋለሁን? አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንም (ገላ 1:10) ።

አንድ ኢትዮጵያዊ የወንጌል ሰባኪ በአንድ መድረክ ላይ ‹‹ተሰማኝ ተሰማኝ ከምትል የሰሚህን ወቅታዊ ችግር አውቅና አክልበት ›› ሲል አድምጫዋለሁ። ዳሩ ግን እውነተኛ የወንጌል ሰው የሰሚውን የልብ ትርታ ማድረስ ሳይሆን የላኪውን ፍቃድ መፈጸም እንደሆነ ቅዱስ ቃሉ ይደግፈናል።

> ሰዎች ሁሉ መልካም ሲናገሩላችሁ ወዮላችሁ። አባቶቻቸው ለሐሰተኞች ነቢያት እንዲሁ ያደርጉላቸው ነበር (ሉቃ 6:26) ።

## ምዕራፍ አስራ አንድ

### የነቢያት ተዓማኒነት

ለዘመኒቱ ቤተክርስቲያን እውነተኛ ነቢያት ያስፈልጓታል፡፡ ያለ ነቢይ ቤተክርስቲያን ለኃጢያትና ለሰው ሃሳብ የተገዛች ትሆናለች፡፡ በአእምሮአዊ አካሄድ ብቻ የእግዚአብሔርን ወቅታዊ የልብ ትርታ ማግኘት አይቻልም፡፡

ቤተክርስቲያን ነቢያትን ካሉበት አስሶ ለማግኘትና ለማስማራት ልትወስድ የሚገባት አያሌ ጥንቃቄዎች አሉ፡፡

በቤተክርስቲያን የምንገኝ ቅዱሳን እውነተኛው የእግዚአብሔር ድምፅ ኮለል ብሎ እንዲወርድልን የሁልጊዜ መሻታችን ነው፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ከሰው አእምሮ ተጨምቆና ተብሰልስሎ እየወጣ ያለው ሰዋዊ ድምፅ ተስፋ ወዳለው መንፈሳዊ አቅጣጫ እየመራን አይደለም፡፡ ስለዚህ በዚህ ወሳኝ የዘመን ሙጣጭ የጌታ ድምፅ የሆኑ ነቢያት ያሹናል፡፡

የነቢያት አገልግሎት ትንሳኤ እያገኘ ባለበት በዚህ ዘመን በዛው መጠን ሀሰተኛ ነቢያትም በየጓዳው ብቅ ብቅ እያሉ በቅዱሳን ዘንድ ግራ መጋባትን እየፈጠሩ ነው፡፡ ብዙ ቅዱሳን በእነዚህ ሀሰተኛ ነቢያት እየተነዱ ከእውነተኛው የእግዚአብሔር ሀሳብ በብዙ እየራቁ ይገኛሉ፡፡ በትንቢት ትዳራቸውን ያፈረሱ፣ በትንቢት ትርፋማ ንግዳቸውን የከሰሩ፣ በትንቢት ቤተክርስቲያንን እንደ ቅርጫ የከፋፈሉ በርካቶች በዚህ ዘመን በተግባር ታይተዋል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛውን የነቢያት አገልግሎትና አካሄዶች ለይቶ ያስረዳናል፡፡ የነቢያትን እውነተኛነት ለመገንዘብ የሚከተሉት መመዘኛዎች በጥናት እናስቀምጣለን፡፡

1. የእግዚአብሔር ጥሪ



ማንኛውም እውነተኛ ነቢይ ጥሪው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፡፡ እግዚአብሔር እውነተኛውን ነቢይ በራሱ ድምፅ ይጠራዋል (ኤር 1:4-10፣ ኢሳ 6:1-8) ፡፡ ነቢዩ ኤርሚያስ እግዚአብሔር ሳይጠራቸው የተሰማሩትን ነቢያት በቅዱስ ቃሉ እንዲህ ሲል ያወግዛቸዋል፡፡

> ቃሉን ያይና ይሰማ ዘንድ በእግዚአብሔር ምክር የቆመ ማነው? ቃሉንስ ያደመጠ፣ የሰማስ ማን ነው? እነሆ የእግዚአብሔር ዐውሎ ነፋስ እርሱም ቁጣው የሚያገለባብጥ ዐውሎ ነፋስ ወጥቷል፡፡ የዓመጸኞችን ራስ ይገለብጣል፡፡ ... እኔ ሳልካቸው እነዚህ ነቢያት ሮጡ፡፡ እኔም ሳልነግራቸው ትንቢትን ተናገሩ፡፡ በምክሬ ግን ቢቆሙ ኖሮ ለሕዝቤ ቃሌን ባሰሙ ነበር፡፡ ከክፉም መንገዳቸው፣ ከሥራቸውም ክፋት በመለሱአቸው ነበር (ኤር 23:19-22) ፡፡

በዘመኒቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ በእግዚአብሔር አምሳል የተወሰደ የነቢይነት አገልግሎትና ከሰው ልብ የተወሰደ (ልብ ወለዳዊ) የነቢያት አገልግሎት አሉ፡፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ የነቢይነት አገልግሎት እጅግ ፍሬያማ ነው፡፡ ሰዋዊው የነቢይነት ጥሪ ደግሞ ማከተሚያው የሰው ፍላጎት ላይ ብቻ ሆኖ ይቀራል፡፡

2. ግብ የመታ ቃል

ነቢያት የሚናገሩት ቃል ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሆነ ይፈጸማል፡፡ የሀሰተኛ ነቢያት ቃል ከሆነ ግን የተፈጻሚነት ስሌቱ ባዶ ነው፡፡

የነቢይ እውነተኛነት የሚለካው የሚናገረው የትንቢት ቃል ተፈጻሚ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ ነቢዩ ሳሙኤል ለዚህ ጥሪ ምሳሌ ይሆናል፡፡

> ሳሙኤልም አደገ፡፡ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበረ፡፡ ከቃሉም አንዳች በምድር ላይ አይወድቅም ነበር (1ኛ ሳሙ 3:19-20)
> ፡፡

ቤተክርስቲያን ለነቢያት ጥሪ እውቅና ትሰጣለች፡፡ ሳሙኤል ራሱን በነቢይነት ቢር አልሾመም፡፡ እግዚአብሔር የነቢይነቱን ጥሪ ካሳወቀው በኋላ መላው የእስራኤል ህዝብ ጥሪውን አረጋግጦለታል፡፡ አገልግሎቱን ሁሉ ተቀብለውለታል፡፡ ምክንያቱም ይናገር የነበረው ትንቢታዊ ቃል ግቡን ይመታ ነበርና፡፡

3. ባህሪይ

ባህሪይ የአንድ ነቢይ እውነተኛነት የመለኪያ መስፈርት ነው፡፡ በማቴዎስ ወንጌል ላይ መልካም ባህሪይ ስለሌላቸው ነቢያት ይህ ማንጸሪያ ቃል ተጽፏል፡፡

> የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ፣ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ከሆኑ ከሀሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ (ማቴ 5:7) ፡፡

በዚሁ ቃል ላይ ተመስርታ ቤተክርስቲያን የተገባ ባህሪይ የሌላቸውን፣ ሥውር ባህሪይን የተላበሱ ነቢያትን ከመካከሏ ማስወገድ አለባት፡፡ መልካም ባህሪይ ሳይላበሱ በተአምራት የደመቀ መንፈሳዊ ክንውኖችን ብቻ ማድረግ የእውነተኛ ነቢይ መልክ አይደለም፡፡



# ምዕራፍ አስራ ሁለት

## የእውነተኛ ነቢያት ምዘና

እግዚአብሔር አምላክ በታሪክ አጋጣሚ ሁሉ ነቢያትን ተጠቅሞ መልካም ፍቃዱን ለሕዝቦቹ ገልጧል፡፡ እውነተኛ ነቢያት ለእግዚአብሔር እውነተኛ መልእክተኛ ሆነው እንደሚነሱ ሁሉ ሀሰተኛ ነቢያትም በታሪክ አጋጣሚ ሁሉ እየተነሱ በእግዚአብሔር ሕዝቦች ላይ ግራ መጋባትን ይፈጥራሉ፡፡ ዳሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስ የእውነተኛ ነቢያትንና የሀሰተኛ ነቢያትን ባህሪይ በማያሻማ መልኩ አስቀምጦልናል፡፡

1. እውነተኛ ነቢይ አይዋሽም፣ የሚናገረው ቃል ያለውን ይፈጽማል፡፡

   የነቢዩ ቃል በሆነ ጊዜ፣ እግዚአብሔር በእውነት የላከው ነቢይ እንደሆነ ይታወቃል (ኤር 28:9) ፡፡

2. እውነተኛ ነቢይ በራሱ ስም ሳይሆን በላከው በእግዚአብሔር ስም ይተነብያል፡፡ ትንቢት ከቶ በሰው ፍቃድ አልመጣምና፡፡ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ (2ኛ ጴጥ 1:21)፡፡

3. እውነተኛ ነቢይ እግዚአብሔር የላከውን መልእክት በራሱ አይሀምር ፍቺ አይሰጥም፡፡

   ይህን በመጀመሪያ እወቁ፡፡ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም በገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም (2ኛ ጴጥ 1:20) ፡፡

4. እውነተኛ ነቢይ ከእግዚአብሔር ሀሳብ ለራቁ ሰዎች ሃጢያትና በደላቸውን ያስታውቃቸዋል፡፡

በኃይልህ ጩኽ፣ አትቆጠብ፣ ድምጽህንም እንደ መለከት አንሳ፣ ለሕዝቤ መተላለፋቸውን ለያዕቆብ ቤትም ኃጢያታቸውን ንገር (ኢሳ 58፡1) ፡፡

5. እውነተኛ ነቢይ ሲመጣ ያለውን የእግዚአብሔርን ቁጣ ያስታውቃል፡፡

ምድር እንደ ሰካር ሰው ትንገዳገዳለች፡፡ እንደ ዳስም ትወዛወዛለች፡፡ መተላለፍዋ ይከብድባታል፡፡ ትወድቃለች፡፡ ደግሞም አትነሳም (ኢሳ 24፡20) ፡፡

በምድርም ለሚኖሩ ለሕዝብም፣ ለነገድም ፣ ለቋንቋም ለወገንም ሁሉ ይሰብክ ዘንድ የዘላለም ወንጌል ያለው ሌላ መልአክ ከሠማይ መካከል ሲበር አየሁ፡፡ በታላቅ ድምጽም፡- የፍርዱ ሠዓት ደርሶአልና እግዚአብሔርን ፍሩ፡፡ ክብርንም ስጡት፡፡ ሰማይንና ምድርንም፣ ባህርንም የውኃንም ምንጮች ለሠራው ስገዱለት (ራእይ 14፡6-7)፡፡

6. እውነተኛ ነቢይ በመንፈሳዊ ጉዳዮች ዙሪያ ቤተክርስቲያንን ቤተክርስቲያንን ያንጻል፣ ይመክራል፡፡

ትንቢትን የሚናገር ግን ለማነጽና ለመምከር፣ ለማጽናናትም ለሰው ይናገራል፡፡ በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል፡፡ ትንቢትን የሚናገር ግን ማኅበረን ያንጻል (1ኛ ቆሮ 14፡3-4) ፡፡

7. እውነተኛ ነቢያት ከቀደሚቸው ነቢያት ጋር ቃላቸው ይስማማል እንጂ አይቃረንም፡፡

ወደ ሕግና ወደ ምስክር ሂዱ! እንዲህም ያለውን ቃል ባይናገሩ ንጋት አይበራላቸውም (ኢሳ 8፡20) ፡፡



8. እውነተኛ ነቢይ ክርስቶስ በሥጋ ወደ ምድር እንደመጣ ይመሰክራል፡፡

ወዳጆች ሆይ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፡፡ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ፡፡ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም መጥተዋልና፡፡ የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚብሔር አይደለም፡፡ ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ነው (1ኛ ዮሐ 4፡1-3) ፡፡

9. እውነተኛ ነቢያት በፍሬያቸው ይታወቃሉ

የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች፣ ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ፡፡ ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፡፡ ከእሾህ ወይን፣ ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማሉን? እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል፣ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል፡፡ መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራት ወይም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም፡፡ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል፡፡ ወደ እሳትም ይጣላል፡፡ ስለዚህ ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ (ማቴ 7፡16-20) ፡፡

10. እውነተኛ ነቢያት ድርጊታቸው ከእግዚአብሔር ፍቃድ ጋር የተያያዘ ነው፡፡

አምላክህ እግዚአብሔር በኮሬብ ስብሰባ ተደርጎ በነበረበት ቀን፣ እንዳልሞት የአምላኬን የእግዚአብሔርን ድምጽ ደግሞ አልሰማ፣ ይህችን ታላቅ እሳት ደግሞ አልይ ብለህ እንደለመንኸው ሁሉ፣ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ፣ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ፣ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል፡፡ በስሜም የሚናገረውን

ቃሉን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልበታለሁ። ነገር ግን ይናገር ዘንድ ያላዘዝሁትን በስሜ በድፍረት የሚናገር ወይም በሌላ የአማልክት ስም የሚናገር ነቢይ እርሱ ይገደል። በልብህም እግዚአብሔር ያልተናገረውን ቃል እናውቅ ዘንድ እንዴት ይቻለናል ብትል ነቢዩ በእግዚአብሔር ስም በተናገረ ጊዜ፣ የተናገረው ነገር ባይፈጸም፣ ባይመጣም፣ ያ ነገር እግዚአብሔር ያልተናገረው ነው። ነቢዩ በድፍረቱ ተናግሮታል፣ እርሱን አትፍራው (ዘዳ 18:15-22)።



# ምዕራፍ አስራ ሦስት

## የሐሰተኛ ነቢያት መገለጫ ባህሪያት

ንቃ ክርስቲያን ንቃ

በሐሰት ነቢያት አትዘናጋ

ያልተማረውን ተመራማሪ

የዚህ ቤት ጌታ ነው ባለ ድግሪ

ያሞካሹታል በዘፈናቸው

ያቺን ሳንቲም እንዲሰጣቸው!

(ከዘማሪት አዜብ መስለ ዝማሬ የተወሰደ)

የበግ ለምድ ለብሰው ወደ ቤተክርስቲያን የሚመጡትን ነቢያት እንዴት ለይቶ ማወቅ ይቻላል? በተለይ የብርሃን መልክ ይዘው የሚመጡትን በምን መንገድ ከቤተክርስቲያን ተመንጥረው ሊወጡ ይችላሉ?

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መጻኢ ሐሰተኛ ነቢያት አስቀድሞ ተናግሯል።

> የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች፣ ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኛ ነቢያት ተጠንቀቁ ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ (ማቴ 7:15-16) ።

ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትም ይነሳሉ። ብዙዎቹንም ያስታሉ (ማቴ 24፡11) ።

ሐሰተኞች ነቢያት ይነሳሉና፣ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክቶችና ድንቅ ያሳያሉ (ማቴ፡24፡24) ።

መጽሐፍ ቅዱስ ሐሰተኛ ነቢያትን ለመለየት የሚያብራሩልን ወደ ሰባት የሚደርሱ ነጥቦች አሉልን።

‹‹ድንቅና ተአምራትን››

ሐሰተኛ ነቢያት በሰዎች ዘንድ አግራሞትን የሚፈጥሩ ዳሩ ግን እውነት አልባ የሆኑ ድንቅና ተአምራትን ሊያደርጉ ይችላሉ። እንዲህ ያለው አድራጎታቸው ምናልባት የተመረጡትን አገልጋዮች እንኳን ከእውነት መንገድ እስከ ማሳት ደረጃ ያደርሳል።

በዚህ አድራጎታቸው ዙሪያ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ሲናገር-

> በመካከልህ ነቢይ ወይም ሕልም አላሚ ቢነሳ፣ ምልክትም፣ ተአምራትንም ቢሰጥህ፣ እንደ ነገርህም ምልክቱ ተአምራቱም ቢፈጸም፣ እርሱም ሄደን የማታውቃቸውን ሌሎች አማልክት እንከተል ቢልህ አምላካችሁን እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችሁ ትወዱት እንደሆነ ሊፈትናችሁ ነውና የዚያን ነቢይ ቃል ወይም ያን ሕልም አላሚ አትስማ (ዘዳ 13፡1-3) ።

‹‹የትንቢት ቃል ስለመፈጸም››



ሌላው የሐሰተኛ ነቢይ መገለጫ ባህሪይ የተናገረው የትንቢት ቃል አለመፈጸሙ ነው።

> ነቢዩ በእግዚአብሔር ስም በተናገረ ጊዜ፣ የተናገረው ነገር ባይፈጸም ባይመጣም፣ ያ ነገር እግዚአብሔር ያልተናገረው ነው። ነቢዩ በድፍረት ተናግሯልና እርሱን አትፍራው (ዘዳ 18፡22) ።

‹‹የተነገረው ትንቢት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነውን?››

ሐዋሪያው ጳውሎስ ሁሉን ነገር በቅዱስ ቃሉ አንጽረን እንድንፈትን ይመክረናል (1ኛ ተሰ 5፡21) ። ‹‹የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳጽ ልብንም ለማቅናት…›› (2ኛ ጢሞ 3፡16) ። ኢየሱስ ክርስቶስም ‹‹መጽሐፍ ሊሻር አይችልምና›› ብሎ ተናግሯል (ዮሐ 10፡35) ። ማንም ነቢይ የእግዚአብሔርን ቅዱስ ቃል ሽሮ የራሱን ትንቢታዊ ቃል በአብላጫ ድምጽ ማቅረብ አይችልም። እውነት ከሆነው ከጌታ ቃል የሚጻረር ቃል የሚያቀርብ ሁሉ ሐሰተኛ ነቢይ ነው። ወደ ሃጢያት ባርነትም ይመራል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ‹‹እውነትም አርነት ያወጣችኋል›› (ዮሐ 10፡32) ብሎ እንደተናገረ የእውነተኛ ነቢይ ቃል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከሆነ አርነት ወደሚሰጥ የህይወት ሽግግር ውስጥ ያስገባል።

‹‹ነቢያት የህይወት ፍሬያቸው ምን ይመስላል?››

በዚህ ጉዳይ ላይ ጌታ ኢየሱስ ሲናገር እንዲህ ብሏል፤

> የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች፣ ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ። ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን፣ ከኩርንችትስ በለስ

> ይለቀማሉን? እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል
> (ማቴ 7፡ 17-18) ።

ክፉ ማንነት ያለው ሰው ክፉ ነገር ያመጣል ብሎ መደምደም ተገቢ ነው፡፡ ስለ የሚባሉ የአስማቶችንና የአገራችንን ነቢያት አስቲ በማስተዋል ህይወታቸውን እንመርምር፡፡ ለምሳሌ አንድ ነቢይ ሁልጊዜ የሚዋሽ ከሆነ እንዴትን አድርጎ የትንቢት ቃሉን መቀበል ይቻላል? አንድ ነቢይ ወጥ የሌለው አቋም ከሌለው እንዴት አድርጎ የሚያስተላልፈውን ትንቢታዊ ውሳኔ ተቀብሎ ማመን ይቻላል? እንዲህ ያለው ነቢይ ሥጋዊ ማንነት አለው፡፡ ሥጋዊ ማንነት ያላቸው ሠዎች ደግሞ የሥጋ ፍሬ እንደሚገለጥባቸው ሐዋሪያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል በቅዱስ ቃሉ አረጋግጧል፡፡

> የሥጋም ሥራ የተገለጠ ነው፡፡ እርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት፣
> መዳራት፣ …ቁጣ…አድመኛነት (ገላ 519-21) ።

ያእቆብ በመልእክቱ የሰማይ መንግስት አገልጋዮች እንዲህ ያለውን ባህሪይ እንደሚባበሉ ይናገራል፡፡

> ምንጭስ ከአንድ አፍ የሚጣፍጥንና የሚመርን ውኃ ያመነጫልን? ወንድሞቼ ሆይ! በለስ ወይራን ወይስ ወይን በለስን ልታፈራ ትችላለችን? ከጨው ውኃም ጣፋጭ ውኃ አይወጣም፡፡ …ላይኛይ ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽሕት ናት፡፡ በኋላም ታራቂ፣ ገር እሺ ባይ፣ ምሕረትና በጎ ፍሬ የሞላባት፣ ጥርጥርና ግብዝነት የሌለባት ናት (ያዕ 3፡11-17) ።

የሥጋ ሥራን እያከናወኑ በነቢያት ስፍራ የተቀመጡ ሠዎች የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋዮች ሳይሆኑ ተቃዋሚዎቹ ናቸው፡፡ ‹‹ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል›› ብሎ ጌታ ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል 12፡30 ላይ እንደተናገረ፡፡



‹‹የሚያሞካሻቸውን መፈለግ››

ሐሰተኛ ነቢያት የሚያሞካሻቸው ሲበዛ፣ እለት እለት ስለሚናገሯት ነገር አድናቆት ከአለም ሰዎች እየተቸራቸው ሲመጣ እነዚህ ሰዎች በእውነት ከእግዚአብሔር የተላኩ ስላመሆናቸው አመራማሪ ነው፡፡ እውነተኛ ነቢያት ሁልጊዜ ‹‹ሕዝብ አስደሳቾች›› አይደሉም፡፡ ዋና ተልእኳቸው የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔርን መልእክት ማድረስ ነው እንጂ በአገልግሎታቸው ዝነኝነትና እንቱታን ማትረፍ አይደለም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ለምሳሌ ስንመለከት ንጉስ አካብ ሊልያስን በእስራኤል ምድር የተቀመጠ ሸብርተኛ አድርጎ ሲቆጥረው እናያለን (1ኛ ነገ 18፡17) ። ንጉስ ፈርዖን የሙሴን ነቢይነት ባለመቀበል አሻፈረኝ ብሏል፡፡ የእስራኤል ሕዝቦችም በተደጋጋሚ ጊዜ አንቀበለህም ብለውታል (ዘኁ 16)፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስም ራሱ እንደ ሰይጣን መልእክተኛ የተቆጠረበትም ጊዜ አለ፡፡ አለም ስለሚያደንቃቸውና የአለም ስለሆኑት ሠዎች ሲናገር ‹‹ሰዎች ሁሉ መልካም ሲናገሯችሁ፣ ወዮላችሁ፡፡ አባቶቻቸው ለሐሰተኞች ነቢያት እንዲሁ ያደርጉላቸው ነበርና›› ብሏል (ሉቃ 6፡26)፡፡

ሀሰተኛ ነቢያት ዝናን፣ ከአለም የሚቸራቸውን እንቱታን ይናፍቃሉ፡፡ ሰዎች ሁልጊዜ ስለ እነርሱ ታላቅነት በየአደባባዩ እንዲናገሩላቸው ይፈልጋሉ፡፡ ይህን ውስጣዊ ጥማታቸውን እውን ለማድረግ ከእግዚአብሔር ያልሆነን ዳረ ግን የሰውን ልብ የሚያስፈነጥዘውን ‹‹መልካም መልካሙን ወሬ›› ለሰዎች ያስደምጣሉ፡፡ ስለ እግዚአብሔር የልብ ትርታ አምብዛም አይጨንቃቸውም፡፡ ማንም ክርስቲያን ወንድም ተነስቶ ስሕተታቸውን እንዲያርማቸው አይፈልጉም፡፡ ይህንን የጠቢቡ ሰለሞንን ምክር አያስተውሉምና፤

> የተገለጠ዗ለፋ ከተሰወረ ፍቅር ይሻላል፡፡ የወዳጅ መሳም ግን
> የበዛ ነው፡፡ (ምሳሌ 27፡5-6) ።

‹‹ስለ ክርስቶስ ያላቸው ግንዛቤ››

ሐሰተኛ ነቢያት ክርስቶስ በሥጋ ፈጽሞ እንደመጣ ይክዳሉ፣ ፍጹም አምላክነቱን በሠማይ ጥሎ እንደመጣ ይሰብካሉ:: በየአደባባዩም ያውጃሉ:: መጽሐፍ ቅዱስ ግን ክርስቶስ በምድር ላይ ሳለ የአምላክነቱን ሥልጣንና ኃይል እያለው ራሱን ‹‹ባዶ›› ሆኖ እንደ እኛው በደምና በሥጋ እንደ ገለጸ ይናገራል::

> በመጀመሪያ ቃል ነበረ:: ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ:: ቃልም እግዚአብሔር ነበረ... (ዮሐ 1-3) ::
>
> እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ፣ ነገር አልቆጠረውም:: ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ፣ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ:: በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ (ፊሊ 2:5-8) ::

ብዙ ሐሰተኛ ነቢያት ጌታ ኢየሱስን ልክ እንደ አንድ ‹‹የሰው የበላይ›› ፍጥረት ያዩታል:: ከሰው በዮት ያለ ባህሪይም ስላለው በምድር ላይ ቀደታው ካጢያት መስራት እንዳልቻለ ያስቡታል:: መጽሐፍ ቅዱስ ግን ለዚህ ከንቱ ሐሳብ ማፍረሻ ይሆን ዘንድ ‹‹ከኃጢያት በስተቀር በነገር ሁሉ እንደኛ የተፈተነ ነው እንጂ፣ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም›› ይለናል (ዕብ 4:15) ::

የእግዚአብሔርን የሕግ ቃል አይጠብቁም

ሐሰተኛ ነቢያት አስተማሪዎች ሁልጊዜ ሠዎችን ከእግዚአብሔር ሕግና ሀሳብ ያርቃሉ:: የእግዚአብሔር የሕግ ትዕዛዛት በአዲስ ኪዳን ስለ ተወገዱ ከእንግዲህ ወዲህ ለመንፈሳዊ ጉዳይ ፈብ የላቸውም ይላሉ:: እነዚህ ሐሰተኛ ነቢያት ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ከማቅረብ ይልቅ በሚሰማሙት ህልምና ራእይ ሠዎችን ወደ



ተሳሳተ መንገድ ያመራሉ:: በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ኃጢያት ተብለው የተፈረጁትን መተላለፎች በአሁን ዘመን ካጢያት እንዳልሆኑ አስረግጠው ይከራከራሉ:: ሐዋሪያው ዮሐንስ ስለ እንደዚህ ዓይነቱ ሐሰተኞች ሲጽፍ ‹‹ኃጢያትን የሚያደርግ ሁሉ ዓመጽን ያደርጋል:: ኃጢያትም ዓመጽ ነው›› ይለናል (1ኛ ዮሐ 1:4) :: ሐሰተኛ ነቢያት ልክ እንደ አባታቸው እንደ ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ ያማቸዋል::

እውነተኛ ነቢያት ግን ለእግዚአብሔር የሕግ ቃል ተገዢዎች ናቸው::

> አምላካችሁን እግዚአብሔርን ተከተሉ:: እርሱንም ፍሩ:: ትእዛዙንም ጠብቁ:: ቃሉንም ስሙ (ዘዳ 13:4) ::

ወገኖቼ እነዚህን ሐሰተኛ ነቢያት ለጥብቀን ከቤተክርስቲያን ለቀመን እናብራቸው:: የሐሰተኛ ነቢያት መገለጫ ባህሪያትን ከቅዱስ ቃሉ ላይ አጥርተን እንወቅ::

# ምዕራፍ አስራ አራት

## የነቢያት ሥልጠና አስፈላጊነትና ማጠቃለያ

በውኑ ነቢያት ልዩ ስልጠና ወይም ትምህርት ያስፈልጋቸው ይሆንን? መጽሐፍ ቅዱስስ ይደግፈን ይሆን? ግልጥ ባለ ቋንቋ በስልጠናቸው ዙሪያ ባያሳስበንም፣ በተዘዋዋሪ መንገድ የአንድ ቀዳሚ «ታላቅ» ነቢይ ተከታይ ወይም ፈለገ-አገልግሎት ዱካ ዳሳሽ እንዲሆኑ ያሳስበናል።

ቀዳሚ ነቢያትን በመጠቀም እግዚአብሔር ለአገልግሎቱ የፈለጋቸውን በርካታ ነቢያትን እንዳሰለጠነ ድርሳነ ሰብና መጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤ ይሰጠናል። እግዚአብሔር ቀዳሚ ነቢያትን ተጠቅሞ ያሰለጠናቸው ነቢያት ብዙውን ጊዜ ለቤተክርስቲያን ሥልጣን የመገዛት ባህሪይ ይታይባቸዋል። በየትኛውም ሥፍራ በእግዚአብሔር መለኮታዊ ሥልጣን ስለጣቸው ቀዳሚ አገልጋዮች መልካም አካሄድ ለመገዛት ፍቃደኞች ናቸው። ያለ ቀዳሚ ነቢያት በራሳቸው ድካምና ብርታት ጎልምሰው የተነሱቱ ነቢያት ግን በየትኛውም ቤተክርስቲያን መለኮታዊ ሥልጣን ለመገዛት እምቢተኞች ናቸው። ምክንያቱም መርሃቸው ያለፉበት ግላዊ የህይወት ውጣ ውረድ ነውና። ይህ አባባል ዳሩ ግን ሁልጊዜ ትክክል ላይሆን ይችላል። እግዚአብሔር ብቻውን በራሱ መንገድ በሚስጥር አሳድጓቸው የሰው ልጆች መፍትሔ የሆኑ እንደ ልዩ ምሳሌ የሚቆጠሩ ነቢያትም አሉ። ሙሴ፣ ኤሊያስና ጌታ ኢየሱስ በምሳሌነት ይጠቀሳሉ። ሦስትም በሀብር እንግዳ የነቢያት ባህሪይ አሳይተዋል። በሰው ልጆች ዘንድ ያልተለመደን አዲስ እንግዳን ገር በሰው ልጆች መካከል አስፋነዋል። ምክንያቱም አሰልጣኛቸው እርሱ ብቻውን በልእልና ለዘላለም የሚኖር እግዚአብሔር አምላክ ነውና።

ታዲያ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ እንዲህ ያሉ ለውጥ አራማጅ ነቢያትን እግዚአብሔር በቀጥታ ማሰልጠን ከቻለ ስለምን ብዙ ጊዜ በብዙ የማስታወቂያ መንገዶች ስለ ነቢያት ስልጠና አስፈላጊነት ይነገራል?



እግዚአብሔር ራሱ ነቢያትን የሚያስለጥንበት ዋና ዓላማ ምድር ላይ አዲስ ለውጥ ይመጣ ዘንድ እንደሆነ ልብ ይሏል። እንዲህ ያሉ ነቢያት በአንድ ውሱን ጊዜ ሰልጥነው በምድር ላይ አይገለጡም። በርካታ ዓመታትን ከእግዚአብሔር ጋር ያሳልፋሉ። መሄድ የሚገባቸውን የህይወት መንገድ እግዚአብሔር አምላክ በትእግስት እንዲሄዱ ያደርጋል። ለምሳሌ ሙሴ በእግዚአብሔር አማካኝነት የሚሰጠውን ነቢያዊ ሥልጠና ለመጨረስ አርባ ዓመታት ፈጅቶበታል።

> በዚያን ጊዜ ሙሴ ተወለደ። ...ሙሴም የግብፆችን ጥበብ ሁሉ ተማረ...ነገር ግን አርባ ዓመት ሲሞላው ወንድሞቹን የእስራኤልን ልጆች ይጎበኝ ዘንድ በልቡ አሰበ።...አርባ ዓመትም ሲሞላ የጌታ መልአክ በሲና ተራራ በምድረ በዳ በቍጥቋጦ መካከል በእሳት ነበልባል ታየው (ሐዋ 7:22፣23፤30) ።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱን ሲጀምር ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ነበር። የእግዚአብሔር ሥልጠና በእድሜ ዘመንን ይወስዳል። አስገራሚው ጉዳይ ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም እንኳን በእግዚአብሔር የሰለጠነ ነቢይ ቢሆንም፣ የእርሱን ዱካ መከተል የሚገባቸው ሴቶች አስራ ሁለት ደቀመዛሙርት ነበሩት። ሙሴ ኢያሱን አሰለጠነ። ኤሊያስ ደግሞ ነቢዩ ኤልሳዕን አሰለጠነ። ሦስቱም ከታላቁ አሠልጣኝ ከሠራዊት ጌታ ከእግዚአብሔር ዘንድ የአሠልጣኞች ሥልጠና (TOT) ወሰደው፣ እንደእነርሱ የበረቱትን ሴቶች ነቢያትን አሰለጠኑ። የእነርሱ ተከታዮችን ለማሰልጠን ብዙ ዘመን አልፈጀም። ምንም እንኳን እነርሱ ሥልጣናቸውን ከእግዚአብሔር ለመቀበል ዘመን ቢፈጅባቸውም።

ዳሩ ግን አሁን ያለነው በዘመን መጨረሻ ላይ ነው። እግዚአብሔር በራሱ መንገድ ለብዙ ዘመን ያሰለጠናቸው በርካታ ነቢያት በምድር ላይ አሉት። ከእነርሱ እግር ሥር ተቀምጦ ሥልጠና መውሰድ ትልቅ ጥበብ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ምጽዓት እየተቃረበ ይገኛልና። ልናጠፋ የምንፈልገው ጊዜ መኖር የለበትም።

> መንፈሱና ሙሽራይቱም፦ ና ይላሉ። የሚሰማም ና ይበል።የተጠማም ይምጣ። የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ (ራእ 22: 17ና 20) ።

በዙሪያችን ያሉትን ነገሮች እንመልከት። ጊዜ እጅግ ይከንፋል። አለም አንድ መንደር ሆናለች። ባለፉት ሃያ ዓመታት ምድራችን አስደናቂ የቴክኖሎጂ ሽግግር አድርጋለች። ልጆችና ወጣቶች በመኖሪያ ቤታቸው ተቀምጠው በቴክኖሎጂ በመታገዝ ሌላ አለም ከሚኖር ሰው ጋር ዝሙት ይፈጽማሉ። የብልግና ምስሎችን ይመለከታሉ። ቤተክርስቲያን ግን ከአገልጋዮችና በነቢያት እጥረት ተመታ ትገኛለች። ቅዱስ ቃሉ *«መከሩስ ብዙ ነው። ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው። እንግዲህ የመከሩን ጌታ ለመከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት» ይለናል* (ሉቃስ 10:2) ።

በዚህ በጊዜ መገባደጃ ላይ ያለች ቤተክርስቲያን በተለይ የቀደሙት ነቢያቶች ይህንን ትልቅ ዓላፊነት መወጣት አለባቸው። «ሀሳች» ነቢያት በመረጃ በተቀነባበረ መረብ አማካኝነት ብቻ ቤተክርስቲያንን ወደ መከራ እየከተቷት ይገኛሉ። ይህ ሁሉ ተተኪ ነቢያትን ለማፍራት ቤተክርስቲያን በመድከሟ እንደሆነ እናያለን።

የነቢያት ሥልጠና በቤተክርስቲያን ውስጥ ሊበረታታ ይገባል። የዘመኒቱ ቤተክርስቲያን ያለ እነርሱ አገልግሎት መዝለቅ ይሳናታል። ሠው ከደረሰበት የአመክንዮ አስተሳሰብ የተነሳ መጽሐፍ ቅዱስን በራሱ አፈታት እየተረጎመ ሃጢያት የሆነውን ድርጊት እያጸደቀ ያለበት ዘመን ቢኖር ይህ ዘመን ነው። የሃጢያትን ገጽታ የእግዚአብሔርን ድምጽ ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር አዳብለው መኮነን የሚችሉት የሰለጠኑ ነቢያት ብቻ ናቸው።

በዚህ ዘመን የሰው ልጅ ከቤተክርስቲያን አገልጋዮች ይልቅ እየደረሰበት ያለውን መንፈሳዊና ሥነ-ልቦናዊ ቀውሶች ለሥነ-ልቦና ምሁራን እያካፈለ ይገኛል። በትላልቅ የሥነ መለኮት ተቋምም መጽሐፍ ቅዱስ ከሥነ ልቦና ትምህርት ጋር ተዳብሎ በመደበኛ ትምህርት መልክ ለተማሪዎች እየተሰጠ ይገኛል። እነዚሁ ተማሪዎች



ተመርቀው ወጥተው፣ እየባሰ የመጣውን የሰው ልጅ ውስጣዊ ችግር ለመፍታት ይሞክራሉ። ሠዎችንም እግዚአብሔራዊ ወዳልሆነ የሥሕተት መንገድ እያጓዟቸው ይገኛሉ።

የሰለጠኑ ነቢያት ጤናማ ባልሆነ መንገድ ያሉችን ቤተክርስቲያንንም የመመለስ መለኮታዊ ጸጋ አላቸው። የክርስቶስ ዓላማ ባልሆነ አካሄድ እየተጓዘች ያለች ቤተክርስቲያንን ጤናማና ፍጹሚውም መልክም ወደ ሆነው ጥሪዋ የሚመልሷት ነቢያቶች ነው። እውቀትና ሰዋዊ አስተሳሰብ በበረከተባት ቤተክርስቲያን መፍትሔዎቹ እነርሱ ብቻ ናቸው። እግዚአብሔር አምላክም በዚህ ተግባራቸው እንዲቆሙ የጸና ቃል በቅዱስ ቃሉ አሰፈግጦ ይነግራቸዋል።

> በጉሮሮህ ጩኽ፣ አትቀጠብ፣ ድምጽህን እንደ መለከት አንሳ፣ ለሕዝቤ መተላለፋቸውን ፣ ለያዕቆብ ቤትም ኃጢያታቸውን ንገር። ነገር ግን ዕለት ዕለት ይሹኛል። መንገዴንም ያውቁ ዘንድ ይወድዳሉ። ጽድቅንም እንዳደረጉ፣ የአምላካቸውንም ፍርድ እንዳተው፣ ሕዝብ እውነተኛውን ፍርድ ይለምኑኛል፣ ወደ እግዚአብሔርም ለመቀረብ ይወድዳሉ (ኢሳ 58:1-2) ።

## ስጋኘ መጻሕፍት


Bickle, Mike, Growing in the Prophetic, Orlando: Creation House, 1996.

Blomgren, Dr. David, Prophetic Gatherings in the Church, Portland: Bible Temple Publications, 1979.

Cramer, Dennis, You Can All Prophesy: Stepping Out with Integrity, Cedar Rapids: Arrow Publications, 2003.

Damazio, Frank, Developing the Prophetic Ministry, Portland: Trilogy Productions, Inc.,1983.

Dufresne, Ed, The Prophet: Friend of God, Tulsa: Ed Dufresne Publications, 1989.

Goll, Jim W., The Seer, Shippensburg: Destiny Image Publishers, Inc., 2004.

Hamon, Dr. Bill, Prophets and Personal Prophecy, Volume 1, Shippensburg: Destiny Image, 1987.

Hamon, Dr. Bill, Prophets and the Prophetic Movement, Volume 2, Shippensburg: Destiny Image, 1990.

Jacobs, Cindy, The Voice of God, Ventura: Regal Books, 1995.

Joyner, Rick, The Prophetic Ministry, Charlotte: Morningstar Publications, 1997.

Price, Paula A., The Prophet's Dictionary, Flaming Vision Publications, 2002.

Randolph, Larry, User Friendly Prophecy, Century City: Cherith Publications, 1995.

Sanford, John and Paula, The Elijah Task, Plainfield: Logos International, 1977.

Thompson, Steve, You May All Prophesy, Charlotte: Morningstar Publications &Ministries, 2000.




